# የተራራው ድምፆች

## የቃል ምስክርነት

### ከወሎ ፤ ኢትዮጵያ



# የተራራው ድምፆች

## የአስረጂዎች ቃል

ከወሎ፤ ኢትዮጵያ

## ርዕሰ አንቀጽ፤

ይህ መጽሐፍ ወደ አማርኛ ከመተርጐሙ በፊት የፓኖስ ተቋም በዓለም አቀፍ ደረጃ ስለአካባቢና ልማት ጉዳዮች ውይይት እንዲካሄድባቸው በማሳሰብ በእንግሊዝኛ ቋንቋ "Voice of the Mountains" በሚል ርዕስ አሳትሞ አሰራጭቶታል።

ይህን መሠረት በማድረግ በኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ድጋፍ

የተራራው ድምጾች

የአስረጂዎች ቃል

ከወሎ፤ ኢትዮጵያ

በሚል ርዕስ ከእንግሊዝኛ ቋንቋ ወደ አማርኛ ተተርጉሞ ታትሟል።

## የኤዲቶሪያል ጭብጦች፤ ፓኖስ ተቋም 2001

ፓኖስ በአለም አቀፍ ደረጃ ስለአካባቢና ልማት ጉዳዮች ውይይት እንዲካሄድ የሚያነቃቃ ተቋም ነው። የፓኖስ ዋና ዋና ጽህፈት ቤቶች ዳካር፤ ካምፓላ፤ ካትማንዱ፤ ለንደን፤ ሉሳካ፤ ፓሪስ፤ ዋሽንግተን ይገኛሉ።

የተራራው ድምጾች በፓኖስ የለንደን የአስረጂዎች ቃል መርሃ ግብር የዓለም አቀፉ የተራራዎች ፕሮጀክት አካል ሆኖ በፓኖስ ተቋም ከሚታተሙ ተከታታይ መጽሐፍቶች አንዱ ነው። የአስረጂዎች ቃል መርሃ ግብር በተለያዩ በደጋማ አካባቢ የሚኖሩ ኅብረተሰቦች አማካይነት ተንታኞችንና ቃለ መጠይቅ አድራጊዎችን በማሳተፍ ለበርካታ አመታት በአጋርነት ሠርቷል። ዓላማውም

## ምስጋና

ይህን መጽሐፍ ለማዘጋጀት መረጃ በማሰባሰብ፣ በመተርጐም፣ ማስታወሻ በመፃፍና ለቃለ መጠይቅ ሁኔታዎችን በማመቻቸት ለተሳተፉ በርካታ ሰዎች ፤ በተለይ አቶ ፈዮራ አብዲንና ሌሎችም የኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ሠራተኞችን እናመሰግናለን። ከሁሉም በላይ ደግሞ ጊዜአቸውን ሰውተው ታሪካቸውን በነፃ ለነገሩን ከፍተኛ ምስጋና እናቀርባለን።

## ስለመጽሐፉ

ቃለ መጠይቆቹ መጀመሪያ ከተሰበሰቡት ተቀንጭበው የቀረቡ ናቸው። አመራረጣቸውም የማወቅ ፍላጐትን የተከተለና እንዲሁም በተቻለ መጠን በአጠቃላይ በኢትዮጵያ የሚገኙ አመለካከቶች ፤ ገጠመኞችና ልምዶችን መወከል እንዲችል ታስቦ ነው። ድግግሞሽ ፤ አላስፈላጊ ጥያቄዎችና ግራ መጋባት እንዳይኖር ፤ ታርመውና ተስተካክለው ቀርበዋል። አንዳንድ የቅደም ተከተል መስተካከል ተደርጓል። ግልፅ ለማድረግ የገቡ ጽሑፎች በዝግ ቅንፎች ተመልክተዋል፣ ትርጉሞችና እንድምታዎች በክብ ቅንፎች ተካተዋል፣ የተቋረጡ አገላለጾች በሦስት ተከታታይ ነጥቦች እንዲመለከቱ ተደርጓል። በቃለ መጠይቁ ውስጥ የገጠሙ ያልተለመዱ ቃላት በጉልህ ተጽፈዋል። የእፅዋት ስሞች በደቃቁ የተፃፉ ሲሆን በተቻለ መጠን ግልጽ እንዲሆኑ ተደርጓል። ሁሉም

ቃለ መጠይቆች የተለያየ የልምድ ደረጃ ባላቸው ሙያተኞች የተተረጉሙ ከመሆናቸውም በላይ ከአካባቢው ቋንቋ ወደ ብሔራዊ ቋንቋ ከዚያም ወደእንግሊዝኛ የተተረጉሙ ስለሆነ አንዳንድ የተዛቡ ነገሮች ሊኖሩ ይችላሉ።

ለአስረጂዎቹ ቃል የተሠጡ ቁጥሮች (ምሳሌ: ኢትዮ.7) ቀሪውን ሙሉ ስብስብ ጽሑፍ የሚያመለክት ሲሆን፦ ያልታረመውንና ያልተስተካከለውን ጽሑፍ ለማየት ፣ ስለፕሮጀክቱ ተጨማሪ መረጃዎችንና አዳዲስ ሁኔታዎችን ለማወቅ ከተፈለገ www.mountainvoices.org. ማየት ይቻላል።

ተከታታይ ጽሑፎች ኤዲተር:Olivia Bennett with Siobhan Warrington;
ኤዲተር: Wendy Davies;
ሕትመት: Norman Smith; conver design: Sally O'Leary;
የሽፋን ዲዛይን: Sarah John;
ካርታ: Julia Colljns; ፎቶግራፎች: Nick Spollin; SOS Sahle (pp21 and 27)

# መግቢያ

በሰሜን ኢትዮጵያ ደጋማው አካባቢ የምትኖር የ38 ዓመቷ ዘውዴ የመሬት ምርታማነት እየቀነሰ መምጣት የማህበረሰቧ ስጋት መሆኑን ስትገልጽ ፡- <<ዛሬ እኩልነት አለ፤ መሬቱ ግን ምርት አይሰጥም>> በማለት ታጠቃልላለች። ሃምሳ ሚሊዮን ከሚሆነው የኢትዮጵያ ህዝብ ሰማንያ ከመቶ በላይ የሚኖረው ከ1500 ሜትር በላይ ከፍታ ባለው ደጋማ አካባቢ ሲሆን፤ ለእርሻ ተስማሚ የሆነ መሬትም በአመዛኙ የሚገኘው በዚሁ ቦታ ነው። በአንጻሩ በበርካታ አገሮች በተለይም ከአፍሪካ ውጭ ያሉ አገሮች ደጋማው አካባቢ አነስተኛ ህዝብ የሚኖርበት ሲሆን፤ ለእርሻም ተፈላጊነቱ ከቆላው ያነሰ ነው። በእርግጥ፤ ከታሪክ እንደምንረዳው የኢትዮጵያ ተራራማ አካባቢዎች የባህል ፤ የፖለቲካ እምብርትና ማዕከል ሆነው ይታያሉ። ይሁን እንጂ በተለያየ የአየር ፀባይ ፤ በተፈጥሮና ሰው ባለማቸው እጽዋት ይታወቅ የነበረው አካባቢ በድርቅ እየተመታ በመምጣቱና በሕዝብ ብዛት በመጣበቡ እየተራቆተ መጥቷል። ብዛት ያለው ህዝብ ተራራዎችን በማረስ የሚኖር እስከሆነ ድረስ የመሬቱ መራቆት እጅግ አሳሳቢ ይሆናል።

በዚህ መጽሐፍ የተካተቱት የአስረጂዎች ቃል የተሰበሰቡት በሰሜን ኢትዮጵያ ደጋማው ክፍል በሰሜን ወሎ አስተዳደር በምትገኘው በመቄት ወረዳ ውስጥ ነው። የሰሜን ኢትዮጵያ ደጋማው አካባቢ ከባህር ጠለል በላይ ከ2000 እስከ 3400 ሜትር ከፍታ አለው። (ካርታውን በገጽ ……… ይመልከቱ)። መቄት ከፍታ ያለው

ደልዳላ የመሬት አቀማመጥ ያላት ስትሆን በስተሰሜን የተከዜ ሸለቆ ያዋስናታል። ተፋሰሱን ተከትሎ የተሰራ የቻይና መንገድ እየተባለ የሚጠራው ጥሩ የሆነ አውራ ጐዳና የሰሜን ወሎን ዋና ከተማ ወልድያን ከወረታ ከተማ ያገናኛል። መንገዱን ተከትሎ ብዙ መንደሮቹና የገበያ ቦታዎች የተቋቋሙ ሲሆን ፤ ከዚህ ሌላ ቀሪው ህዝብ ከመንገድ ወጣ ብለው በሚገኙት ደልዳላ ቦታዎችና በሸለቆው ላይ ባሉት የእርሻ ማሳዎች ጥግ ተከታትለው በሚታዩት መንደሮች ይኖራሉ።

አንፃራዊ በሆነ አነጋገር ወሎ ብዛት ያለው ሕዝብ ያለበት ነው። የህዝቡ መተዳደሪያ ሙሉ በሙሉ ለማለት ይቻላል በግብርናና በከብት እርባታ ነው። ይሁን እንጂ ባለፉት ሃያ አመታት መሬቱ በከፍተኛ ደረጃ እየተራቆተ በመሄዱ በቂ ዝናብ በሚጥልበት ዓመታት እንኳ ምርቱ በጣም አስተማማኝ አልሆነም። ምንም እንኳን የልማት ወኪሎች ከህዝቡ ጋር በመሆን ግባዓቶችን በማቅረብ የተራቆተውን አካባቢ ለመመለስ ጥረት ቢያደርጉም ህብረተሰቡን ከድህነት ሊያላቅቁት አልቻሉም። አስገራሚ ባይሆንም የአስረጂዎቹ ቃል የሚያጓጓና ሰዎች ስለወደፊቱ ያላቸውን ስጋት እና እንዲሁም በማንነታቸውና በቅርሶቻቸው የሚመኩ መሆናቸውን ያመለክታል።

<u>ጭብጥ</u>

ግብርና በአስተማማኝነት ቀጣይ አለመሆን ቁልፍ የስጋት ምንጫቸው ነው። ለምርት መቀነስ የተጠቀሱት ልዩ ልዩ ምክንያቶች ከዝናብ እጥረት፣ በደርግ ዘመነ መንግስት በተደረገው የመሬት

ክፍፍል ከተሰጡት አነስተኛና የተበጣጠሱ ማሳዎችና ከሕዝብ ብዛት ጋር የተያያዘ ነው። የደን መራቆት የሰፋ በመሆኑ የማገዶ እጥረት አስከትሏል። የአፈር መሸርሸርን አባብሶታል፤ የዱር አራዊትና እንስሳትን መጥፋት አፋጥኗል። አብዛኞዎቹ ተናጋሪዎች የሚያወሱት ያሳለፉትን ከባድ ገጠመኝ ፤ በፍጥነት እያሻቀበ የሄደው የኑሮ ግሽበት እና አስፈላጊ የሆኑ እቃዎችን ለመግዛት ከብቶቻቸውን መሸጥ ግዴታ እንደሆነባቸው ነው።

ሌላው ፍሬ ነገር ለብዙ ዘመን የቆየው በችሮታና በልግስና የተመሰረተው የእንግዳ አቀባበል፤ ለአረጋዊያንና ለአካል ጉዳተኞች ይሰጥ የነበረው እንክብካቤና ኃላፊነት ባህል እየቀነሰ መምጣት ነው። ለዚህም ዋነኛ ምክንያት የሚያካፍሉት ሃብት የሌላቸው መሆኑ ነው። የመሬት ክፍፍሉ እኩልነት ያመጣ በመሆኑ በበጐ ጐኑ ቢያዩትም ፤ በቤተሰብ ደረጃ መሬት እየተበጣጠሰ በመምጣቱ የነበራቸውን የቤተሰብ ትስስርና የጋራ ታሪክ እየቀነሰ እንዲሄድ ያደረገ ስለሆነ አልወደዱትም። አሁን ባለው ሁኔታ እያንዳንዱ ቤተሰብ ከዘመድ ብዙ ድጋፍ ሳይጠብቅ የየራሱን የወደፊት ኑሮ ማመቻቸት ላይ እያተኰረ መጥቷል።

ብዙ ሰዎች ትምህርት፤ የልማት ሥራዎች በተለይም የደን ልማት እና ሙያዎችን መማር የወደፊት ኑሮአቸውን ለማሻሻል እጅግ በጣም አስፈላጊ መንገድ እንደሆነ ያምናሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የወሊድ ቁጥጥር ማድረግ የህዝብ እድገትን እንደሚቀንስ በአጽንኦት ይናገራሉ። ብዙዎቹ ተናጋሪዎች ጥሩ ለውጦች ይታዩባቸዋል ከሚሏቸው መካከል ሴቶች በህብረተሰቡ ያላቸው ደረጃ ከፍ ማለት፤ በክርስቲያኖችና በእስላሞች እንዲሁም በሌሎችም ያለው መልካም

ግንኙነት፣ በጤና ፣ በትምህርትና በመገናኛ የተደረጉ መሻሻሎችን ይጠቀሳሉ። አንዳንዶቹ ደግሞ የሚገልጹት በስፋት ከቦታ ቦታ መዘዋወሩ የኤድስ ስርጭትን ሊያስፋፋ ይችላል የሚል ስጋት ነው። በአጠቃላይ የኅብረተሰቡ መገለልና እንዲሁም ዜናን ለማዳመጥ፣ መረጃ ለማግኘት፣ አዳዲስ ሃሣቦችን ለመገብየት አመቺ ሁኔታ አለመኖር የእድገት ማነቆ እንደሆነ ተደጋግሞ ተገልጿል።

## የሥራ አጋርነትና ፕሮጀክቱ

ፓኖስ ከ1992/93 ጀምሮ በመቄት ሲሰራ ከቆየው ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ኢትዮጵያ ጋር በመተባበር ሠርቷል። አካባቢው መልሶ ለማንሰራራት በማይችልበት ሁኔታ ከፍተኛ የአካባቢ መራቆት አደጋ የሚታይበት፣ በየወቅቱ የምግብ እጥረትና ረሃብ ያለበት ነው። ኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል ያለመው ገበሬዎችን ከምርምር ተቋማት ጋር በማገናኘት የቴክኒክ አማራጮችንና ስልቶችን ሙከራ ለመርዳት እና የአካባቢያዊ ተቋማትን አቅም ለመገንባት ነው።

እነዚህ የአስረጂነት ቃሎች የተሰበሰቡት ከታህሳስ 1996 እስከ ጥቅምት 1998 ባለው ጊዜ አሁን የመቄት የልማት ፕሮጀክት እየተባለ በሚጠራው ፕሮጀክት ላይ ካሉት በአመለወርቅ መብራት፣ በእንዳልካቸው ያረጋል፣ በብርሃኑ አበበ ይመር ፣ በመስፍን ኢያሱ፣ በአስቴር ደርቤ እና በወንዳየ ወንዴ ነው። አላማውም የቃል አስረጂነት እንደ ምርምር ዘዴ በመጠቀም የመስክ ሠራተኞች ኅብረተሰቡን ያሳተፈ ምርምር የሚያካሂዱበትን ችሎታ ለማዳበር ነው። እንዲሁም ሰራተኞችና የአካባቢው ኅብረተሰብ በአንድ ላይ

በቅርበት ተገናኝተው በተወሰኑ ፍሬ ነገሮች ላይ ያላቸውን ልዩ ልዩ ልምድና አስተያየት እንዲለዋወጡ ፤ ከዚያም በአማርኛ አነስ ያለች መፅሐፍ ለማሳተም እንዲቻል እድሉን ለመስጠት ታስቦ ነው። ምንም እንኳ የምስክርነት ቃሎቹ ቢጠናቀሩም በኢትዮጵያ በተከሰተው ድርቅና ያልተቋረጠ ግጭት ምክንያት ኤስ.ኦ.ኤስ ሳሀል ኢትዮጵያ ትኩረቱን በተጐጂዎች እርዳታ ስራ ላይ ስላደረገ የህትመት ስራው እንዲዘገይ ሆኖአል።

## የአስረጂዎች ቃል

**አዘኑ** ኢትዮ.11

አዘኑ የ45 ዓመት ጉልማሳና የቤተሰብ ኃላፊ ስትሆን ነዋሪነቷ በመቀርቀሪት ነው። ለመጠየቅ እድል ማግኘቷን በዐጋ ነው የተቀበለችው። ምክንያቱም የጥያቄና መልስ ሂደቱ ህብረተሰቡ <<ጥንት ቀደምት አባቶቻችን ይመሩት የነበረውን ህይወት ሊመራ ያስችለው ይሆናል>> የሚል ስሜት ስላሳደረባት ነው። በእርሷ አመለካከት አሁን ያለው ችግር ሊቃለል የሚችለው እፅዋትን በማጽደቅና የአፈርን መሸርሸር በመቋቋም ነው። በዚህ መልኩ አካባቢው ይለወጣል ትላለች።

መቀርቀሪት ቆንጆ ናት ። ቁንጅናዋንም እንዲህ እያሉ ያደንቃሉ።

መቀርቀሪት የምድር ህይወት፣

የምድር ገነት ፣

እዚህ በተወለድሁ

ወይም በተጋባሁ

የቆንጆ (ሴቶች) መገኛ ናት።

ልጆቻችሁን ዳሩ (አጋቡ) መቀርቀሪት ካሉት

እኔ ሕፃን እያለሁ ደግሞ እንዲህ ይሉ ነበር ፣

ልጃችሁን የት ነው የዳራችኋት ?

ታጉባ።

ለምን ታጉባ? መቀርቀሪት ለማድረግ ስትችሉ፣ ይባል ነበር።

አሁንም ድረስ በጅርቤና ቀላበስ የሚኖሩ ሰዎች በዚህ ሁኔታ ይቀናሉ። ምክንያቱም እዚህ ውሃው ጥሩ ነው፣ መሬቱ ለም በመሆኑ ሌሎች ገበያ ወጥተው ወርደው የሚገዟቸውን እንደ ሽንኩርት ፣ ቃሪያ፣ ጫት ፣ አብሽ፣ ጌሾ የመሳሰሉትን በጓሮ በመትከልና በመዝራት ማግኘት ይቻላል። ገበያ ለመሄድ የምንገደደው ጨው ለማግኘት ብቻ ነው። በተጨማሪ አሁንም አካባቢው ሲለማ ልክ እንደ ቀድሞው መሬቱ ምርታማ ነው።

እኛ በጓሮአችን በቀላሉ የምናገኘው ጉመን ወደ ከተማ ብትሄድ አንድ ጭብጥ የምታክለውን እንኳ በአስር ሳንቲም መግዛት ይኖርብሃል። ሁኔታዎች ከተሻሻሉ / ከተመቻቹ በሶስት ወይም በአራት ዓመታት ጊዜ ውስጥ ራሳችንን እንችላለን፣ ከስደትና ከረሃብም ለመዳን እንችላለን። እዚህ ብዙ ሊበሉ የሚችሉ እንደ

አሳማ ያሉ ቅጠላ ቅጠሎች ይገኛሉ ይሁን እንጂ እንደ አረባል ያሉ ምንም አረንጓዴ ነገር የማይታይባቸው ስፍራዎች አሉ።

## እየተባባሱ የሄዱ ሁኔታዎች


መቀርቀሪትን የጐዱት የሕዝብ ብዛት መጨመር ፤ የአየር ፀባይ መለዋወጥና የአፈር ብክለት ወይም መሸርሸር ናቸው። በየተዳፋቱ የሚወርዱት ጅረቶች አለቶችን እየገለበጡ በማምጣት ስለቀለሏቸው ፍየሎቻችን እንዳይገድሉብን ስጋት ላይ ጥለውናል። ሆኖም ዛፎቹ እያደጉ ሲሄዱ ሁኔታው በቁጥጥር ስር ይውላል...

በድሮ ጊዜ ደኑ በደንብ የተጠበቀ ስለነበረ ለማገዶ የሚሆን አንድ ሸክም እንጨት ከአንድ ዛፍ ማግኘት እንችል ነበር። አሁን ግን ዛፎቹ ተመንጥረው በማለቃቸው መሬቱ ተራቁቶ ምድረ በዳ በመሆኑ አንድ ሸክም የማገዶ እንጨት ለማግኘት ረጅም ርቀት በመሄድ ቀኑን ሙሉ መድከም ይኖርብሃል። አፈሩ ለወራጅ የጐርፍ ውኃ የተጋለጠ ነው፤ ትላልቅ ጅረቶች ቀደም ሲል ባልነበሩባቸው ሥፍራዎች እየታዩ ነው። የዱር አራዊት ጠፍተዋል። የሕዝብ ብዛትም ጨምሮ መሬቱም ጭራሽ ምርት አልሰጥ ብሏል።

> የከብት ርባታ
> በልጆች ርባታ
> ተተክተል።

ከብቶች የሚግጡት ሣር አጥተው በተራቆተ መሬት ላይ ተኩልኩለው ስለሚውሉ በረሃብና በበሽታ እያለቁ ናቸው። ቀደምት አባቶቻችን ዘመን በአንድ ጥንድ መሬት ትንሽ ማሳ አርሰው አስር አህያ ጭነት እህል ያገኙ ነበር። አሁን ግን በዚሁ መጠን ባለው ማሳ ሶስት አቁማዳ እህል ማግኘት አይቻልም። ሃብታም የሚባሉት ጥቂት ሰዎች እንኳን የቀራቸው ትልቅ ቤትና አጥር ብቻ ነው። ቀደም ሲል

የማናውቀው እህል ዳጉሳ በነጋዴዎች መጥቶ ለምግብነት እየተጠቀምንበት ነው። በዝናብ እጥረት ምክንያት መስኖ እየቀነሰ መጥቷል። የሕዝብ ሃብት እየተሟጠጠ፣ የልጆች ቁጥር እየጨመረ በመሄዱ የእንስሳት እርባታውን ተክቷል ለማለት ይቻላል።




ጥንት መኖ በብዛት ስለሚገኝ እንስሳት መኖውን ሣያሟጥጡ መጋጥ ይችሉ ነበር። ደኑ ባለመመንጠሩ፣ ሣይታረስ የሚተው መሬት በመኖሩ... እንስሳት የሚመገቡት ከዚያ ይገኝ ነበር። በመሆኑም እንስሳት ማርባት ቀላል ነበር። [አሁን] ግን ያ ሁሉ ቀርቶ ከጠራራ ፀሐይ... ሊጠለሉበት የሚያስችል ጥላ እንኳን የለም።

## የችግር ጊዜ እና ተስፋ

[ደርግ] በገመድ እየለካ ያከፋፈለው መሬት አንድን ቤተሰብ ለመመገብ የሚያስችል አይደለም። ይህም ሆኖ ልጆች መሬት አይሠጣቸውም፤ መሬቱም እህል አያበቅልም። ሦስት አቁማዳ እህልም ለአመት አይበቃም። ከሰኔ እስከ መስከረም ያለው ጊዜ ሰቆቃና ሞት ያለበት በመሆኑ ላይም ወጥተህ ታችም ወርደህ በግ በመሸጥ ዳጉሳ መሸመት አለብህ። ከዚህ ሰቆቃ ለመላቀቅ የምናደርገው ሌላ ምንም አማራጭ የለም።

እኛ ልጆች እያለን 7 ላዳን እህል ባንድ ብር ይሸመት ነበር። ከአንድ እስከ ሁለት ላዳን የሚሆን እህልም በሃምሣ ሣንቲም ይገኝ ነበር። አሁን አንድ ቆርቆሮ ዳጉሳ ለመግዛት 3.50 ይጠይቃል። አምስት ወይም ስድስት የቤተሰብ አባላትን ከሰኞ እስከ አርብ ለመመገብ የማይበቃውን አንድ ቆርቆሮ ጤፍ ለመግዛት ከአምስት እስከ ስድስት ብር ይጠይቃል። የራሴንም ሆነ የቤተሰቤን ንጽህና ለመጠበቅ የሚያስችለንን ሳሙና ለመግዛት ካልቻልኩ መታመማችን አይቀሬ ነው። ይህን ችግር ሁሉ ሳስብ እበሳጭና እታመማለሁ።


የአካባቢውን ገጽታ ለመቀየር የመሬቱን መሸርሸር ለማቆም ክትሮች እየተሰሩ ችግኞች እየተተከሉ በመምጣታቸው ደስ እያለኝ ነው። ጅረቶቹ በድንጋይ ተሞልተው አፈር እየሞላ ከሄደና ችግኞቹን በመትከል የአፈሩን እጥበት ለመከላከል ከተቻለ የአካባቢው ሁኔታ ስለሚቀየር ለእርሻ ጠቀሜታ ሊውል ይችላል።

ጤና ጣቢያ ፤ ንፁህ የመጠጥ ውሃ ፤ ትምህርት ቤት የተሠሩልን ሲሆን የመንገድ ስራና በማሳዎቻችን ላይ የእርከን ግንባታ ተጀምሮልናል። እንዲሁም ራሳችንን ለመርዳት እንዲያስችለን በቃጫና በበግ ፀጉር አሠራር ትምህርት ተሰጥቶን ምንጣፎችንና ዘንቢሎችን እየሰራን ለኤስ.ኦ.ኤስ ኃላፊዎቻችን በማቅረብ በእነሱ በኩል በየወረዳው እየተሸጡ ድርሻችንን እየወሰድን ነው። ከእንግዲህ ያሉብን ችግሮች እየተቃለሉ እንደሚሄዱ ተስፋ አለን።

## ለሴቶች የተደረጉ ለውጦች

በድሮ ጊዜ ሃብታም ወላጆች ያሏቸው ልጃገረዶች የሚፈለጉት ቆይተው ነበር። እንደ ምሳሌ እኔ ራሴን ብወስድ ከዚህ ሰፈር ተወልጄ ወደ ታጉባ ስዳር ባለቤቴ ብዙ ከብትና እህል ጉተራ ያለው እንዲሆን ካለመጠየቄም በላይ ጥሎሽ አምጣ አላልኩም። ሁሉም ያልም የነበረው የስንዱልን ልጅ ለማግባት ነበር። ማርና ወተት የሞላበት ቤቴንም ምንም በእጄ ሳልይዝ ለቅቄ ወጣሁ። ከፍች በኋላም አንድ ወር እንኳን ሳንቆይ እጮኛ ዳግም ይመጣልናል።

አሁን ግን ወንዶች ትዳር ለመመስረት ሲፈልጉ አስቀድመው ከብትና እህል ወይንም ሌላ ሃብት እንዳላት ካላረጋገጡ ለትዳር አይጠይቁም።



<<ይህ ነው መሬታችን>>

ድሮ ከቤታችን ሳንርቅ ከማዕድ ቤት እና በማጀት ሆነን እህል እየፈጨን ምግብ እያበሰልን ፣ ልዩ ልዩ የቤት ሥራዎችን እየሰራን እንውል 'ነበር። በጣም የተጨቆንን ስለነበርን ባሎቻችን ከሥራ ወደ ቤት ሲመለሱ ሥራ ኖረንም [አልኖረንም] እግራቸውን እንድናጥባቸው ያስገድዱን ነበር። በደርግ ጊዜ ደግሞ መሠረተ ትምህርት ስለተጀመረ፣ አንዳንድ ሴቶች ከማጀት ወጥተው በመማራቸው ከሚኖሩበት ቦታ ርቀው ሥራ ፍለጋ ሲሄዱ በማየታችን እኛም ቅናት ስለተሠማን መማር ጀመርን። ወንዶችም

እኛን አይ ነው ከሴቶች ወደ ኋላ ለመቅረት ሥላልፈለጉና በአውራ ጣታቸው ከመፈረም ለመላቀቅ ሲሉ መሠረተ ትምህርት ገቡ።

ቀደም ሲል የሴቶች የስራ ጫና በጣም ከባድ ስለነበረ አስልቺ የሆነውን ልዩ ልዩ የቤት ሥራ ከመስራት በተጨማሪ ልጆችን የመንከባከብና የማሳደግ ከፍተኛ ኃላፊነት የተጣለው ለሴቷ ነው። አሁን ግን ትምህርት እየተስፋፋ ስለሄደ ምንም እንኳ እኔ ልጆች ባይኖሩኝም የእናቶችና የልጆች ህይወት እየተሻሻለ መጥቷል።

## ያረጋል

ኢትዮ. 19

ያረጋል ነዋሪነቱ ዋርቃዬ ሲሆን 41 ዓመት የሞላውና የዘጠኝ ቤተሰብ ኃላፊ ነው፤ ሚስቱ ፤ አራት ልጆች፤ የቤት ሠራተኛ በእርሻ የሚረዳውና የከብት እረኛ አሉት። ቃለ ምልልስ የተደረገው ድብቆ በምትባል ከተማ በገበያ ቀን ስለነበረ ቃለ ምልልሱ በገበያተኞች ድምጽ በተደጋጋሚ ይቋረጥ ነበር። ያረጋል የሚሰማው የድህነቱ ጫና በመቄት የሚኖሩ ሰዎች እንደሚያይል ነው። መሬታቸው እየተጣበበ ወይም ምርታማነቱ እየቀነሰ በሄደ ቁጥር የልጆቹ የወደፊት ህይወት በትምህርት ላይ የሚመሠረት ይሆናል የሚል እምነት አለው።

> *መላኩ (ወንድ፤ 67 ዓመት እድሜ) መምሬ* ኢትዮ 17
> ሰውየው ትዕዛዝሰጠ፤ እግሩን እንድታጥብና ውሃም እንድትቀዳለት ጠየቃት። እሷም ባዘዛት መሠረት አከናወነችለት። አሁን እኩልነት አለ ቢባልም እንደቀድሞው ነው፤ ወንዱ ያዛል፤ ሴቷም ትዕዛዙን ትፈጽማለች።
> *መኩንን (ወንድ፤ 72 ዓመት እድሜ) መምሬ* ኢትዮ 16
> በአሁኑ ጊዜ ወንዶችእየተጨቆኑ ነው። የሴቶች ቁጥር በዝቷል እና ወንዶች፣ እየተሰቃዩ ነው። ቀደም ሲል ሴቶች እህል ይፈጩ ነበር፤ አሁን ግን ሥራ ፈትተው ይንገላወዳሉ።

በድሮ ጊዜ በባላባታዊው ሥርአት አንድ ሰው የቀኝ አዝማችነት ወይም የግራ አዝማችነት ማዕረግ ካገኘ መሬት ይሰጠዋል። ይህን መሬትም እንደ አሽከር ሆነው በሚያገለግሉት በጭሰኞች እያሳረሰ በክብር ይኖር ነበር። ባላባቱ ያለ እርሱ ፈቃድ በመሬቱ ላይ ማንም ሰው ዝር እንዳይል፣ በእግሩም እንዳይረግጠው ይከለክለው ነበር። የአሁኑ አስተዳደር ግን ሰው ከሰው ሳይለይ ማዕረግ ሳይመለከት መሬቱም ለሁሉም እኩል በማከፋፈሉ ምስጋና ይገባዋል። ይሁን እንጂ ያለው መሬት በቂ አይደለም፣ ዝናብም ወቅቱን ጠብቆ አይመጣም።

በአራት ወይም በአምስት ዓመት ልዩነት የተወለዱ አራት ልጆች አሉኝ። ከእርሻው የሚገኘው ምርት አነስተኛ ስለሆነ ሁሉንም ልጆቼን ትምህርት ቤት አስገብቻቸዋለሁ። ሁሉም ከተማረ ልማትም ሆነ ገበያ ይስፋፋል የሚል ተስፋ አለኝ። በአካባቢያችን የተቋቋመው የጤና ጣቢያ ከፍተኛ ጥቅም እየሰጠን ነው። ቀደም ሲል ያጠቃን የነበረው የወባ ትንኝ አሁን እየቀነሰ ሄዷል። ዶክተራችን ሙሉጌታ በበሽታ የምታጠቃንን የወባ ትንኝ እንዴት እንደምትራባ ፣ በምን አይነት መንገድ ልትጠፋ እንደምትችል ስላስተማረን አሁን እኛው ራሳችን የራሳችን ዶክተር በመሆን የወባ ትንኟን እያጠፋን የልማት ስራችንን እያካሄድን ነው። የግብርና ሠራተኞችም ሰብላችንን ያወድሙብን የነበሩትን ተባዮች ለምሳሌ እንደ ዶጋዛ ፣ ፌንጤራ የመሳሰሉትን እንዴት እንደምናጠፋ አስተምረውናል። አሁን ያሉብን ችግሮች በቆላማው አካባቢ የተዘራውን ማሽላ የሚያጠፉ ወፎች፣ በረዶና ድርቅ ናቸው።

> የወባ በሽታ ለማከም እኛ የራሳችን ዶክተሮች ሆነናል።

በግብርና ቢሮው ረዳትነት ከብቶቻችን ሲታመሙ ኪኒን የሚሰጡልን ፣ መርፌ የሚወጉልን የከብት ሃኪሞች ስለተመደቡልን የከብቶቻችን ጤና እየተሻሻለ ነው። ቀደም ሲል ግን የከብት ሃኪም አልነበረንም።

መስኖን በተመለከተ በቂ ውኃ የለንም፣ ሕዝባችን ጠንካራ ሰራተኛ ነበር፣ በመስኖ ለመጠቀም ልዩ ልዩ ዝግጅቶችን ያደረገ ቢሆንም ውኃው ግን ይደርቃል። ከዚህ ዝቅ ብሎ ወርቃዬ በሚባል ቦታ ከአምስት እስከ ስድስት ሺህ እግር ቡና በመስኖ አልምተው ገበሬዎች በመጠቀም ላይ ናቸው። ያም ሆኖ አሁን ውሃው እየጠፋ ነው። የውሃ እጥረት ባይኖር ኖሮ ፓፓዬ ፣ ሎሚ፣ ብርቱካንና ሙዝ እናለማ ነበር።

## ለአቅመ ደካሞች የሚደረግ እንክብካቤ

በከተሞች አካባቢ መንግስት አይነ ስውራንንና አካል ጉዳተኞችን አሰባስቦ እየጦራቸው ነው። በድሮ ጊዜ ረዳት የሌላቸው አቅመ ደካማ አረጋውያንን እያንዳንዱ በሠፈር ያለ ቤተሰብ ተራ በመግባት በየቤቱ እየወሰደ በመመገብ ይጦራቸው ነበር። አሁን ግን በገጠር በተንሰራፋው ድህነት ምክንያት ገበሬዎች ረዳት የሌላቸውን አረጋውያንን ለመደገፍ ችላ እያሉ መጥተዋል። የቤተሰብ ትስስሩም እየላላ መጥቷል።

> ቤተሰባዊ ትስስሩ እየላላ መጥቷል።

## የመቄት ሰዎች

የመቄት ሰዎች ንቁዎች ናቸው። በክብረ በአላት ጊዜ የሚይዟቸው የክብራቸውም ምልክት የሆኑ ጠመንጃዎችና ሰጋር በቅሎዎች አሏቸው። አሁን አሁን እየደኸዩ መጡ እንጂ ቀደም ሲል ቤታቸው ሲኬድ እንግዳ አቀባበላቸው፤ ዘፈናቸው ፤ የሙዚቃ መጫሪያዎቻቸውና አዝማሪዎቻቸው የራሳቸው መታወቂያ የሆነ ልዩ አይነት ነበሩ። አሁን ግን የድህነት ጫናው እየበዛ ስለሄደ ቀደም ሲል የነበረው ዘፈናቸውና እስክስታቸው ባለማንሰራራቱ ሞቅ ያለ የቤተሰብ መንፈሳቸውን አልመለሰውም። እናቶች ልጆቻቸውን የሚመግቡት አጥተዋል። የቤተሰብ ትስስርም እየላላ መጥቷል። አሁን ህዝቡ ተስፋ እያደረገ ያለው እግዚአብሔር ምህረቱን አውርዶላቸው እንዲታረቃቸውና የተሻለ ምርት እንዲሰጣቸው ነው።

አሁን አሁን እንደ ጥምቀት ባሉ የአውደ አመት በአላት ላይ ነው ሰዎች ሲጨፍሩ፤ ሲዘፍኑ የፈረስ ግልቢያ (ጉግስ) ሲያደርጉ የሚታየው። በሰርግ ላይ እንዲህ እያሉ ይዘፍናሉ።

> በአገራችን ቆንጆዎች ብዙ ናቸው፤ ጀግኖችም ብዙ ናቸው፤
> ጠመንጃ ለማግኘት ነው እኛ የመጣነው ፤
> የእኛ ጌታ ሸልመን ፤ ሸልመን ፤ ሸልመን ፤
> ያማረ ነው ልጃችን ፤ ማራኪ ነው ልጃችን፤

ሙሽራው ሙሽሪትን ይዞ ሲወጣ ወይዛዝርቱና ጠና ያሉ ሴቶች ሲሸኙዋቸው እንዲህ እያሉ ይዘፍናሉ

ሸኘኋት ፤ ሸኘኋት ፤
ሸኘኋት ፤ ሸኘኋት ፤
የብር ዋንጫዬን ሰጠኋት

እንደሚታየው የመቄት ሰዎች በሰርግም ሆነ በሌላ የደስታ ጊዜ የሚጫወቱበት የበለፀጉ ባህሎች አሏቸው።

## አዳዲስ ክሂሎችን መማር


በኤስ.ኦ.ኤስ ሳህል የተመደበ አቶ ጥላሁን የሚባል አሰልጣኝ ስለ ዘመናዊ ንብ ርባታና ቀፎ አሰራር ለአንድ ሳምንት ያህል አሰለጠነን። ከዚያ በኋላ እኔ በበኩሌ ስለ ዘመናዊ ንብ እርባታና ዘመናዊ ቀፎ አሰራር ሌሎችን ገበሬዎች በማስተማር ገቢ ማግኘት ችያለሁ።

ቀደም ሲል የሠራተኛ ችግር ካለባቸው ሴቶች ጋር በእርሻ፤ በአረም፤ እህል በመሰብሰብ እያገዝኳቸው ድርሻዬን ተካፍዬ ለመውሰድ ተስማምተን ነበር ፤ ይሁን እንጂ የሚገኘው ምርት የመሬቱ ባለቤት ለዘር ያወጣውን እንኳ የማይመለስ እየሆነ መጣ። ነገር ግን አንድ ሰው በንብ እርባታ ቢሰማራ አንድ ብርጭቆ ማር በስድስት ብር፤ አንድ ማሰሮ ማር ካለው ደግሞ እስከ ሰባት መቶ ብር ሊሸጥ ይችላል። ይህም ብዙ ጉልበት ሳይፈስ ንቦቹ ወደ ሰው ማሳ ሄደውብኛል ብሎ ሳይጨነቅ የሚሠራው ነው። በዚህ ሥራ የሚገኘው ገንዘብ ለአመት ቀለብ የሚሆን እህል ለመሸመቻና ልጆቹን ወደ ትምህርት ቤት ልኮ ለማስተማሪያ የሚበቃ ይሆናል።



<<ለመቄት ሰዎች ጠመንጃ፤ በቅሎና የመሳሰሉት የክብራቸው ምልክት ናቸው>>

ትምህርት ጠቃሚ ነው። የተማሩ ሰዎች የምናየው ከሌላ ቦታ ወደዚህ ተመድበው ለመንግስት ወይም ለኤስ.ኦ.ኤስ ሲሠሩ ነው።



ማሕበራዊ ተቋማት

እነኚህ ጠግበው በልተው በሥራ ምክንያት እንደኛ እጃቸው ሳይሻክር፣ ለስልሶ አምሮባቸው እናያለን። ይህ መሬታችን ነው፣ ይሁን እንጂ መሃይም ገበሬዎች ሆነን እዚሁ ቀርተናል። ማንም ሰው ከዚህ በግብርና ተወስኖ ልጆች እያሳደገ ኑሮውን የሚመራ የተረገመ ነው እላለሁ።

ሰዎች ትምህርት ላይ አትኩረዋል።

ሴት ልጄ ብታገባ እወዳለሁ ፣ ምክንያቱም ወደ ትምህርት ቤት ከገባች ፣ ከአንዱ ጋር ፍቅር ይይዛትና ልትኮበልል ስለምትችል ለቤተሰቦቿ ሃፍረት ትሆናለች። ወንድ ልጅ ግን እንዲማር እፈልጋለሁ። ከተማረ ትልቅ ሰው ስለሚሆን ራሱን ረድቶ እኛን ወላጆቹንም ሊረዳን ይችላል። በጋብቻ በኩል የመረጠውን ሊያገባ ይችላል።

<<መፍትሔው ትምህርት ነው>>

ቀደም ሲል የጤና ኬላ ባለመኖሩ አንድ ሰው ከታመመ መሞት ብቻ ነበር። አሁን ግን ትምህርት ቤት ተከፍቷል፣ ጤና ጣቢያም ስለተቋቋመ ሰው ቢታመም ሕክምና ለማግኘት ይችላል። ይህን ሳያዩ የሞቱት ዘመዶቻችንን ስናስታውሳቸው ያሳዝኑናል። መንግስትም ይህን ስላደረገልን ምስጋና ይገባዋል። በሕዝብ ብዛት የተነሳ መሬቱ እየተጣበበ መጥቷል። ለዚህ ደግሞ መፍትሔው ትምህርት ነው። አንዳንድ ሰዎች እየተማሩ ሹፌሮች ፣ መምህራን ፣ የጤና ሠራተኞች ፣ የመንግስት ሰራተኞች እየሆኑ ከግብርና ስራ እየሸሹ ነው። እኛ ቀደም ብለን ባለመማራችን እያዘን ከመሬቱ ጋር ተጣብቀን ቀረን። አንድ ገበሬ በምትሰጠው ቁራጭ መሬት የመኖሪያ

ቤት ሰርቶ ከመቀመጥ ሌላ ምንም ሊያደርግበት አይችልም። ስለሆነም ሰዎች አሁን ከቁራጭ መሬት መጣበቃቸውን አይተው ፊታቸውን ወደ ትምህርት አዙረዋል።

በ1984/85 በተከሰተው ረሃብ ፤ እኔ እኖር የነበረው ከሃብታም ቤተሰብ ጋር ነበር። በዚያን ወቅት ጉረቤቶቻችን ከመሬት የወደቀ አጥንት ሲግጡ በአይኔ በብረቱ አይቻለሁ ። በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ፊታቸውን ወደ መስኖ በማዞር ቡና በመትከል፤ የጋራ እርሻ በማረስ ፤ ልጆቻቸውን ወደ ትምህርት ቤት በመላክ እንዳለፈው ጊዜ በችግር ወድቆ ላለመሰቃየት ጥረት እያደረጉ ናቸው።

## አይቼሽ

ኢትዮ.1

አይቼሽ፤ እድሜዋ 28 ሲሆን በሆነ ወቅት የትውልድ ከተማዋን ጋላ ደጀንን ትታ ከሄደች በኋላ የተወለደችበትን ቦታ ስለምትወድ ተመልሳ የመጣች ናት። ቃለ [illegible] ባማደረግበት ጊዜ ልጇዋን የሚይዝላት ስለሌለ አዝላ ነ[illegible]። በሰፌድ ላይ ካለ[illegible] ስንዴ ቆሻሻ እየለቀመች ነበር የምትናገ ው። በልጇዋና በለ[illegible]ች ሰዎች ጣልቃ ገብነት ንግግሯ በተደጋጋሚ ይቋረጥ ነበር።

ለምግብ የሚሆን ምርት ነው? የምን ለምግብ የሚሆን ምርት ነው የምትለው? ምንም የለም። በድሮ ጊዜ በርከት ያለ ዋሰራ ይመረት ስለነበር ብዙ ምግብ ነበረን። አሁን ግን ህይወታችንን ለማቆየት ያህል ከሌላ ቦታ በቆርቆሮ እየተሰፈረ በሚመጣ ዳጉሳና ገብስ ነው የምንኖረው። በአሁኑ ጊዜ በእኛ አካባቢ ምርት የሚጠብቅ አለን? በድሮ ጊዜ መሬት በአባቶቻችን እጅ ሆኖ በቂ ነበር ፤ ዝናብ

በበቂ ሁኔታ ስለሚጥል መሬቱም ምርታማ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ዝናብ የለም፤ ዝናቡ ጥሎ ቡቃያው አደገ ስንል እንደገና ከባድ ዝናብ ይጥልና አዝመራውን ያጠፋዋል። ምርቱ ይቀንስና ምግቡም ጣዕም የለሽ ይሆናል።

ህፃናት በግብርና ላይ የተመሠረተ ኑሮ እንዲመሩ ያደረገ ማንም ሰው የተረገመ ነው።

እንደ ዛሬው ብዙ ሰው ሳይኖር ፤ ዱሮ ፤ አያቶቻችንና ቅድመ አያቶቻችን ያልተያዘ ቦታ ፈልገው በማረስ የራሳቸው ካደረጉ በኋላ እነርሱ ሲያልፉ ልጆቻቸው እየተተኩ በመውረስ ይጠቀሙበት ነበር። መሬቱም የእነ እንቶኔ መሬት ነው እየተባለ ከትውልድ ትውልድ ይተላለፍ ነበር። መሬቱም ሰፊ፤ የህዝቡም ቁጥር አናሳ ነበር። ደርግ ሲመጣ ደግሞ መሬት የሕዝብ ነው በማለት ለሁሉም እኩል ስለአከፋፈለ፤ አንዳንድ ድሃ ሰዎችን መሬት እንዲያገኙ በማድረግ ጠቅሟቸዋል። ምንም እንኳን አባቶቻችን ለአንዳንዶቻችን ሰፋፊ መሬት ትተውልን ቢያልፉም አሁን ያለን ቁርጥራጭ መሬት ነው። እኔን እንደ ምሳሌ ብትወስዱ ለእርሻ መሬት ተብሎ የተሰጠኝ ለአንድ ጦጣ ለአንድ ቀን የማይመግብ ነው።

መሬቱ በውሃ እየታጠበ ስለሄደ ምርታማ አልሆን ብሏል። አንድ ሰው ደሙ እየተመጠጠ ካለቀ እንደሚሞት ሁሉ መሬቱም እንደዚህ ሆኗል። አሁን ትንሽ ምርት የሚያገኙ ሰዎች ማዳበሪያ የሚጠቀሙ ናቸው፤ አራት መቶ ብር በብድር ተሰጥቶኝ ለማዳበሪያ መግገርያ ብወስድ ገንዘቡን መልሼ ለመክፈል ከየት አመጣዋለሁ? እህል፤ በግ ፤ ፈረስ፤ በቅሎ ፤ ላም ካለ እነዚህን በመሸጥ እዳውን መክፈል ይቻላል። አሁን የሚታየው ግን እንኳንስ እዳ ለመክፈል ቀርቶ የሚበላም እያጣ ነው።

## የወደመው ደን

አባቴ እንደነገረኝ ከሆነ እረኛ በነበረበት ወቅት ይህ አካባቢ ጥቅጥቅ ያለ ደን እንደነበረውና እርሱና ጓደኞቹ ጊዜያቸውን እዚህ ያሳልፉ እንደነበር ነው። በደኑ ውስጥ እንደ ነብር ያሉ የዱር አራዊት ስለነበሩ ሰዎች በዚህ ለማለፍ አይደፍሩም ነበር። በዚህ የሚያልፉት የቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን መነኩሴ ብቻ ነበሩ። ደኑ መሬቱ እንዳይታጠብ ይጠብቀው ነበር። ለምሣሌ አንድ ሰው በጣም ሲከሳ ገፉ ብታደርገው ፍንግል ይላል። መሬቱም ከተራቆተ እንደዚሁ ስለሚሆን እየተዳከመ ሄዶ ምርት አይሰጥም።

ለእርሻ እየተባለ ዛፎች ሁሉ ስለተመነጠሩ የዱር እንስሳት እንደ ነብር ፣ ዝሆን ፣ ዝንጀሮ፣ ናሜ ፣ እባብ ሳይቀር ጠፍተዋል። ደን ወዳለበት ስለተሰደዱ በቆላማ ቦታዎች እንኳን ሳይቀር አይታዩም።

ወሳኙ ሁኔታ የዝናቡ ወቅት ነው።

ሰዎች ለቤት መስሪያና ለማገዶ ሲሉ ዛፎችን መድምደዋቸዋል። እንደዚህ ሰው እየበዛ ሲሄድ እንጨት የት ይገኛል? ከባህር ዛፍ በስተቀር ሌላ ዛፍ አይታይም። ሌላ አማራጭ ስለሌለ አንድ ሰው የማገዶ እንጨት ለማግኘት ከፈለገ ባህር ዛፍ መትከል ይኖርበታል። የባህር ዛፍ አድጉ ጥቅም ላይ ለመዋል ከሦስት እስከ አምስት አመት ይጠይቃል። ስለሆነም ገንዘብ ኖሮኝ ባህር ዛፍ ገዝቼ ለመጠቀም እስካልቻልኩ ድረስ ያለኝ አማራጭ ደን ሄዶ ዛፎችን መቁረጥ ብቻ ነው።



ግብርና

## እየተመናመነ የመጣ የከብት ርባታ ፤ ባዶ ጉተራዎች

ደርግ እንዳይወርሰው በመስጋት አጉታችን 120 በጐችን ይዞ እዚህ መጥቶ ነበር። አንድ ሰው ከሰባት እስከ ስምንት የሚደርሱ ላሞችን በአንድ ጊዜ ወልደው ይጠግት ነበር። የግጦሽ መሬቱ ከአባት የተወረሰ ሆኖ ከ40 እስከ 50 የሚደርሱ እምቦሳዎች በአንድ ወቅት ይወለዱ ነበር። አሁን አንድ ላም እንኳን ያላቸው ጥቂቶች ናቸው። ከዚህም በላይ በቂ መኖ ስለማያገኙ ሦስት ላሞች ታልበው ቀደም ሲል አንድ ላም ትሰጥ የነበረውን ወተት ያህል አይሰጡም። ቀደም ሲል እያንዳንዱ ሰው ከከብቶቹ የሚያገኘውን ቅቤ ለራሱ እየተጠቀመ አይቡን እንግዳ ሲመጣበት ያስተናግድበታል። አሁን ግን አንድ ላም እንኳን ኖሮህ ቅቤ ብታገኝ ለራስ ከመጠቀም ይልቅ በማግስቱ ያችን አነስተኛ ቅቤ ጠፍጥፎ ወደ ገበያ በመሮጥ በሃምሣ ሣንቲም ወይም በአንድ ብር ሸጦ ይመለሳል። በድሮ ጊዜ የእያንዳንዱ ሰው ጉተራ፤ በጤፍ ፤ በገብስ ወይም በምስር የተሞላ ስለነበር ቅቤ መሸጥ አስፈላጊ አልነበረም።

ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ በሰኔ ስለማይጥል ሰዎች ችግሩ ከዚህ የመነጨ ነው ይላሉ። ለምሣሌ ባለፈው አመት ዝናቡ ዓመቱን በሙሉ ጥሏል። ይሁን እንጂ ለእንስሳቱም ሆነ ለእህል ጥሩ አልነበረም። አሁን እንደምታዩት ዳመናው ተንጠልጥሏል፤ ከዘነበ ግን እህሉን ያጠፋል። ይህ ግሉባል እየተባለ የሚጠራው የኤክስቴንሽን መርሃ ግብር አራት መቶ ብር አስከፍሎናል። ከባድ በረዶ ጥሎ እህሉን ስላወደመው ሰዎች ባዶ እጃቸውን ቀርተዋል።



ግብርና 1

ድሮ አባት ለልጆቹ የእርሻ ማሳዎችንና የግጦሽ መሬት ይሰጥ ነበር፤ አሁን ግን [የግጦሽ መሬት] እንደ እርሻ መሬት ተለክቶ ተከፋፍሏል። በአሁኑ ጊዜ እኔ ከብት ስለሌለኝ የግጦሽ መሬት ለመጠየቅ አልችልም። ይህ ከብት ላላቸው ብቻ የተፈቀደ ነው።

እንደተነገረኝ አባቴ በሌለበት እናቴ 31 ከብቶቿ ስለሞቱባት ራሷን በማንጠልጠል ሕይወቷን አጠፋች። ልጄ ሻሂና ዳቦ ያደገበት ስለሆነ ይወዳል። አሁን እኔ እጄ አጥሮ ለመግዛት ባልችል ችግሬን ይረዳልኝ ይመስልሃል? በዚህ ዓይነት ምክንያት ነው እናቴ ህይወቱን ለማጥፋት የቻለችው።

## የግብርና አሠራር

የእርሻ ወቅት የአካባቢው ሁኔታ ላይ የተመሠረተ ነው። በቆላማ አካባቢ ከሆነ በመጋቢትና በግንቦት ማሽላ ይዘራል። አካባቢው ደጋ ከሆነ ደግሞ በግንቦትና በሰኔ ምስር ይዘራል። ከዚያም በማከታተል አተር ፤ ባቄላ፤ ስንዴ፤ ወሰራ (ይህ በዚህ አካባቢ ብቻ የሚበቅል ነው) ይዘራል። ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ጥሩ ከጣለ ምስር ጥቅምትና ህዳር የሚሰበሰብ ሲሆን ሌሎች ደግሞ የተዘሩበትን ወር ቆጥረው በተከታታይ ይሰበሰባሉ። ወሳኙ የዝናብ ሁኔታ ስለሆነ ዝናብ ወቅቱን ጠብቆ ካልመጣ እስከ ጥር ድረስ ምንም ዓይነት እህል አይዘራም። ማንኛውም ነገር ከተስተካከለ ደግሞ ከመስከረም ጀምሮ የተዘሩበትን ጊዜ እየቆጠሩ ይደርሳሉ።

| | |
|---|---|
| መለስ (ወንድ 45 ዓመት) | ኢትዮ 20 |

በቀድሞ ጊዜ አንዲት እናት 5 ወይም 6 ልጆች ሊኖሯት ይችላሉ። በከፊተኛ የሰብል ምርት ምክንያት ቤተሰቡ የተትረፈረፈ ሃብትና ንብረት ነበረው። እናትም ልጆቿን ትወዳቸዋለች፤ ትንከባከባቸዋለች። አሁን በአንድ ቤተሰብ ብዙ ልጆች ይወለዳሉ። እናት ሁሉንም ቤተሰብ መቀለብ ይሣናታል። ምግብ እንድትሠጣቸው ሲነዘንዟት እናት ትጠላቸዋለች። ልጆቹም ቤተሰባቸውን ጥለው ለሌሎች ሠዎች አገልጋይ ይሆናሉ። አንዱ የባል እና ሚስት መለያየት መንስኤ ልጆችን መመገብ አለመቻል ነው። በመጨረሻም ጋብቻው ይፈርስና ሁሉም ይሠደዳሉ።

መሬት የሌላቸው ደግሞ ነጋዴ በመሆን፣ ለአዲሱ መንገድ ምስጋና ይግባውና ወደ ወልድያ በመኪና በመሄድ ሸቀጦቻቸውን እንደ ቡና ፣ ስኳር፣ እንቁላል፣ ላምባ፣ ቅቤ የመሳሰሉትን እያመጡ ይሸጣሉ። እንጨትም እንዲሁ ይሸጣሉ። ድሮ እንቁላልም ሆነ እንጨት እንዴት ይሸጣል? ይህን ማድረግ በጣም አሳፋሪ ነበር።

## የኅብረተሰቡ መደጋገፍ

በአካባቢያችን ማኅበር ፣ ሰንበቴ፣ እቁብና ቅሬ [አለን]። ድሮ አንድ ሰው ከጋላ ደጀን ወይም ከመቀርቀሪት ሲሞት ሁሉም በቀብሩ ስነ ሥርዓት ይገኝ ነበር። የሟቹን ቤተሰብ ለማስተዛዘንም ከያለበት ቦታ ማለት ከጋላ ደጀን ፣ ከመቀርቀሪት በማሰሮ ወጣችንን በመሶብ እንጀራችንን ይዘን እንሄድ ነበር። የሞተው ሰው የቅሬው አባል ነው አይደለም ተብሎ አይጠየቅም ነበር። ደርግ ወደ ስልጣን እንደመጣ ግን ይህ ሁኔታ ተቀይሮ አንድ ሰው ሲሞት የሞተው ሰው የቅሪያችሁ አባል ስለሆነ ከቀብሩ ስነ ሥርዓት እንድትገኙ የሚል ጥሪ ስለሚተላለፍ፣ የሚገኙት የቅሬው አባላትና የቅርብ ዘመዶቹ ናቸው። በማስተዛዘኑም በኩል የሚተባበሩት የቅሬው አባላት ብቻ ናቸው። በሠርግ ዝግጅትም ቢሆን ለደጋሹ በግ ፣ ጠላ፣ በድጋፍ መልክ ከተወሰደለት ፣ በሌላ ጊዜ ስጦታ አድራጊው ሲደግስ ውለታው ይከፈለዋል። ነገሩ እንካ በእንካ ነው።

ማኅበር ሲወርድ ሲዋረድ ከጥንት ከአባቶቻችን የመጣ ስርዓ ነው። የማኅበሩ አባላት ከአስራ ሁለት እስከ አስራ ሶስት ሆነው ተራ በተራ እየተቀባበሉ ፤ ለእያንዳንዱ አባል በዓመት እንደሚደርስ ሆኖ ድግስ ይደግሳሉ። እንግዶቹ በደጋሾቹ ቤት ለሦስት ቀናት ሲበሉና ሲጠጡ ከቆዩ በኋላ ይሄዳሉ። እነሱ እንደሄዱ ጉረቤት ተጠርቶ ይጋበዛል።

> አሁን ይህ እኩልነት የሚባል ነገር መጣ።

ሰንበቴ እሁድ እሁድ በቤተ ክርስቲያን ቅጥር ግቢ አባላቱ ተሰብስበው በባለተረኛ አባል ጠላና ዳቦ የሚጋበዙበት ነው። ግብዣው እንደተጠናቀቀ ተረኛው ማን እንደሚሆን ከተነገረ በኋላ የሚቀጥለው ዝግጅት እንዲያደርግ ቆሞ ይመረቃል። እሱም ቀጣዩን ዝግጅት በማድረግ ጊዜው ሲደርስ ይጋብዛል። ባህሉ ቢኖርም የዝግጅቱ/የድግሱ መጠን ግን ተለውጧል። አንድ ሰው እጁ አጠሮ ለማዘጋጀት ካልቻለ ሰንበቴውን ጥሎ መውጣት ይችላል። ድሮ አንድ ሰው ሰንበቴ ሲያወጣ በግ አርዶ አራት አምስት አይነት ወጥ አሰርቶ በትላልቅ ጋኖች ጠላ አስሞልቶ ካዘጋጀ በኋላ ማኅበርተኞቹን ወደ ቤት በመውሰድ ለሶስት አራት ቀን ይጋብዛቸው ነበር። አሁን ግን እንደ አቅምህ በአንድ እንስራ ጠላና ዳቦ ልትሸኛቸው ትችላለህ...

[የአካባቢው ኅብረተሰብ ይረዳዳል ወይ?] አዎ ለምን አይረዳዳም? ለምሳሌ እስላሞች ወደ ቤተ ክርስቲያን አይሄዱም።ነገር ግን ሰው ሲሞት ወደ ሟቹ ቤት በመሄድ አዘንተኛውን ያስተዛዝናሉ። አንድ ሰው እንደ አጋጣሚ ሆኖ ያልተጠበቀ ችግር ቢያጋጥመውና እርዳታ የሚያስፈልገው ቢሆን አንድ ባህር ዛፍ እንኳ ቢኖረኝ ያንን

ሽጩ መርዳት አለብኝ። በአንድ ላይ የምንኖር የአንድ አገር ሰዎች በመሆናችን እንረዳዳለን።

አንድ ሴት መሬት ኖሯት ማረስ ካልቻለች ወንዶች ያርሱላታል። ሴቶች ደግሞ ተሰብስበው አረም ያርሙላታል። መሬት የሌላት ሆና ምግብ ለማግኘት የማትችል ከሆነ ኅብረተሰቡ ተራ በተራ እየወሰደ ይመግባታል። ታማሚ ሆና የሚንከባከባት ካጣች ደግሞ ማኅበረሰቡ ተራ ጥሎ በየቤቱ እየወሰደ እየመገበ አስታሞ ከሞተች በወግ ይቀብራታል። ይህ ባህላችን ነው።

በድሮ ጊዜ ፍቅር፣ ስምምነት ስለነበረ ሰዎች ስሜታቸውን ሳይደብቁ ስለሚገልጹ ትስስሩ ጥብቅ ነበር። አሁን ግን ለይስሙላ አብረው እየተረዳዱ መኖር ነው። ድሮ ሴቶች ከባሎቻቸው ጋር ወደ እርሻ ቦታ በመሄድ ሲረዱ ከዋሉ በኋላ ቀድመው ወደ ቤታቸው በመመለስ ለባሎቻቸው ጠላና ምግብ አዘጋጅተው ይቆዩ ነበር። አሁን ይህ እኩልነት የሚባል ነገር ስለመጣ ባሏ አንድ ነገር እንድታደርግ ሲጠይቃት አልታዘዝም ትላለች። ሁለቱም የግብርናውን ስራ እኩል መሸከም መቻል አለባቸው።

<<በአንድ አምላክ እናምናለን>>

አምልኮ የምናደርገው በቤተ ክርስቲያኖቻችን ነው። እኛ የምናምነው በአንድ አምላክ ነው። በሌላ ጣኦቶች አናመልክም። በእርግጥ ቅዱስ የሆነውን ታቦት ቀርበን ለማየት ባንችልም በእርሱ ስም የተባረከውን ነገር እንሳለማለን። ለምሣሌ በቅዱስ ጊዮርጊስ ቅጥር ግቢ ያለውን የዕድ ዛፍ ብሳለም እግዚአብሔርን እንዳመለኩ

እቆጥረዋለሁ። አምልኮአችን ከጥንት ሲወርድ ሲዋረድ የመጣ በመሆኑ ምንም አዲስ ነገር የለበትም። በክብረ በዓል ታቦቱ ከቤተ ክርስቲያን ሲወጣ፤ ቆንጆ ቆንጆ ልብሶችን ለብሰን ወንዶች የፈረስ እሽቅድምድም በማድረግ በደማቅ ሁኔታ እናጅባለን።

በአሁኑ ጊዜ ሰዎች ፊታቸውን መነቀስ ትተዋል። በጥሩ ስፌት የተሰናዱና ያሸበረቁ ቀሚሶች ከከተሞች የተወሰዱ ናቸው። ድሮ ወንዶች ከጥጥ የተሰሩ ቁምጣ ሱሪዎችን ነበር የሚታጠቁት። አሁን ግን ወደ እርሻ ቦታም ሆነ ወደ ስብሰባ ሲሄዱ ዘመናዊ ሱሪዎችን እየታጠቁ ነው።

## የመገናኛ አውታሮች

[ዘመናዊ ትምህርት ቤት] የተሰራበት ቦታ በጣም ሩቅ ስለሆነ የአምስት አመትና የስድስት አመት ህፃን እዚያ ልኮ ለማስተማር አይቻልም። ይህን ማድረግ ቀኑን ሙሉ ጊዜን በመንገድ ማሳለፍ ማለት ነው...

> ሬዲዮ ያለው የለም።

አንድ ሰው የሞተ እንደሆነ ከእያንዳንዱ መንደር የቅርብ ዘመድ ተፈልጎ ይነገረውና በሌሎች መንደሮች ያሉት ሰዎች እንዲሰሙ ይደረጋል። የሰማው በተራው ደግሞ ኮረብታ ላይ ወጥቶ ድምፁን ከፍ በማድረግ እንቶኔ ሞቷልና ለቀብር እንድትገኙ በማለት መልዕክቶቹን ያስተላልፋል። ሰርግ ከሆነም በዚሁ መልክ የሚተላለፍ ሲሆን 20 ቀን ያህል ቀደም ብሎ በመናገርና ደብዳቤ በመላክ ይሆናል። ማኅበር ከሆነ ደግሞ

ወደ ዘመዶችና ጐረቤቶች ልጅ በመላክ ወይም ደግሞ ራስህ በቤተክርስቲያን ወይም በገበያ ቦታ ... እንዲሰሙ በማድረግ ነው።

ከተማው ገና አላደገም፤ ሬዲዮ ያለው የለም፤ እንደነገርኩህ ወሬ የምናገኘው ቤት ክርስቲያን ፤ ገበያ ቦታ ስንሄድ ወይም ከሃዘን ቦታ ስንሄድ ነው።

ሕፃን በነበርኩበት ጊዜ ወደ ደላንታ፤ ከሰከሴ ለመሄድ የምጓዘው በእግሬ ነበር። መንገድ አልነበረም። ሰዎች የራሳቸውን ስንቅና ለከብቶቻቸው መኖ ይዘው እየተጓዙ ጫካውን በረሃውን አቋርጠው ለሣምንትና ለወር ያህል ይጓዙ ነበር። አንዳንዶችም በየመንገዱ እየሞቱ ይቀሩ ነበር። አሁን ግን ቻይናዎቹ ይህን መንገድ ስለሠሩልን ማንም ሰው ሃብታም ሆነ ደሃ ረጅም ርቀት ያለውን መንገድ በመኪና ተጉዞ ጉዳዩን ፈጽሞ በማግስቱ ሊመለስ ይችላል።

<u>በላይ</u> ኢትዮ.7

በላይ የ41 ዓመት ገበሬና አንጥረኛ ሲሆን ነዋሪነቱ ዳባ ጊዮርጊስ ነው። ግብርናና አንጥረኝነት ሙያ በማወቁ እና እንዲሁም ማንበብና መፃፍ በመቻሉ ኩራት እንደሚሰማው ገልጾ ቀደም ሲል በአንጥረተኞች ላይ የነበረ ንቀት መቀነሱን፤ በክርስቲያኖችና በእስላሞች መካከል ያለው ግንኙነት መልካም መሆኑን ይናገራል።

ምንም የሚመረት ባለመኖሩ ቀደም ሲል በርካሽ ይሸጥ የነበረው አሁን በጣም እየተወደደ መጥቷል። ለምግብ የሚሆን እህል ቢኖርም ጥቂት ነው። የለም ማለትም ይቻላል። ከብቶች መኖ

አጥተው እንደተራቡት ሁሉ ንቦችም እፅዋት ስለወደሙ የሚቀስሙት አጥተው ማር ሊሰሩ አልቻሉም። በዚህ የተነሳ የማር ዋጋ እጅግ እየናረ መጥቷል። አፈሩ በጉርፍ እየታጠበ በመሄዱ መሬቱ ጅረቶች እያበጀ ነው። ከብቶች መኖ ሊያገኙ የሚችሉበት ጫካ ነበር። በመሆኑም ገበሬዎች ከ15-20 የሚደርሱ ፍየሎችን ያደልቡ ነበር፤ አሁን ግን ጫካው ለእርሻ ስለተመነጠረ ፍየሎች የሚመገቡት ስለማያገኙ ሁለት ወይም ሶስት የደለቡ ፍየሎች ያለውን ሰው ፈልጉ ማግኘት አዳጋች ነው።




<<ዛፎችን ማሳደግ፤ እርከንና የአፈር መከላከያ ግድቦችን መስራት ጠቃሚ ሆንዋል።>>

[በድሮ ጊዜ] የፍየል ጋጣዬ ስለጠበበኝ አንዳንድ ፍየሎች እና በጉች ከመጠለያ ውጪ በጨለማው ያድሩ ነበር። በዚያን ጊዜ ቢያንስ ቢያንስ 45 ወይም 46 በጉች ፤ ከዚህ የሚበልጡ ፍየሎችና አንድ

በቅሎ ፣ ሁለት ጥንድ ብሬ እና አህዮች ነበሩኝ። ከዚህ በተጨማሪ እህል እየተከፈለ የሚያርሱ ገበሬዎች ስለነበሩኝ ብዛት ያለው እህል ነበረኝ። አሁን መሬቱ ወደ እርሻ ስለተቀየረ የግጦሽ መሬት እየጠፋ በመሄዱ ያሉኝ ሰባት ወይንም ስምንት ፍየሎች ፣ አንድ በግ ከነግልገሏል፣ ሁለት ላሞች ፣ ሦስት በሬዎች ብቻ ናቸው። ቀደም ሲል አምስት አህዮች ነበሩኝ። አሁን ግን በቅሎዬንም ሸጨ የቀረኝ አንዲት አህያ ብቻ ናት። ድሮ ጠፍ በሆነው መሬት ላይ የሚበቅል ነጭ ሳር የሚባል ስለነበረ ያ ሲደርቅ በሰኔ ለከብቶች መኖ ይሆን ነበር። አሁን ግን ከብቶች የሚግጡት እጻሪ ቦታ ስለሌለ አንድ ገበሬ ለከብቶቹ የሚሆን መኖ ለማግኘት ከርሻው ድንበሮች ያበቀለውን ሣር እያጨደ በመሰብሰብና በመኸር ወራት ደግሞ ገለባውንና ተረፈ ምርቱን ካላጠራቀመ ለከብቶቹ የሚሆን መኖ ጭራሽ አያገኝም።

መሬቱ ለእርሻ ስለዋለ እየታጠበ በመሄድ ጅረቶች እንዲበዙ ስላደረጋቸው ምርት ለማግኘት አልተቻለም። ይህች [አሁን እኛ የተቀመጥንባት] መሬት እንደምታያት ሣር ይታይባታል። ምክንያቱም ባለቤቷ ሰነፍ ሆኖ ሳያርሳት በመቅረቱ ይሆናል። ታርሳ ቢሆን ኖሮ እንደ ሌላው መሬት በጉርፍ ታጥባ ሳርም አታበቅል ነበር። አንዳንድ ገበሬዎች እኔም ጭምር በአለታማ ቦታዎቹና በአንዳንድ ይዞታዎቻችን ላይ መስኖ በመጠቀም ቡና ፣ ጌሾ ፣ሙዝ እያለማን ነው። አንዳንድ ሰዎች ደግሞ ዳጉሣ የሚባለው አዲስ መጤ እህል ጥሩ ምርት እያስገኘ ነው ስለተባለ በስፋት እየተዘራ ነው።

ደኖች
ለእርሻ
ተመንጥረዋል።



ባህላዊ ክህሎት

## የለውጥ ተስፋ

ምንም የጤና ጣቢያ እዚህ የለም፤ ይሁን እንጂ ሐኪሞች ወደ መንደራችን መድሃኒት ይዘው በመምጣት የታመሙትን ያክማሉ። መንግስት ትምህርት ቤት ስለከፈተ ብዙ ሰዎች እተማሩ የማንበብና የመፃፍ ችሎታቸውን አዳብረዋል። እኔ ራሴ ማንበብና መፃፍ ችያለሁ። አረባል በተባለው ስፍራ አዲስ ትምህርት ቤት ስለተከፈተ ብዙ ወጣቶች ገብተው እየተማሩ ናቸው። ተማሪዎቹ እስከ ስድስተኛ ክፍል ተምረው ትምህርታቸውን ሲጨርሱም፤ በተማሩት ትምህርት ምንም ጥቅም ሳያገኙ ስራ አጥ ሆነው ይታያሉ። ቢሆንም ብዙ ሰዎች ትምህርት በማግኘታቸው መንግስትን እያመሰገኑ ነው።

አሁን አዳዲስ ትምህርት ቤቶች በየአካባቢው ስለተከፈቱ እንደምገምተው ወጣት አዛውንት ሳይል የሚማር ይመስለኛል። ጉርፋን ለመቆጣጠር ከተቻለና መሬቱ በቂ ምርት መስጠት ከቻለ ለውጥ ይኖራል እላለሁ። ጤና ጣቢያ ከተቋቋመና በቂ መድሃኒት ማግኘት ከተቻለ ሰዎች ጤናማ ይሆናሉ፤ ለውጥም ይኖራል።

## ክህሎችና ትምህርት

ከአባቴ በተማርኳቸው የማረስና የእንጥረኝነት ክሂል እንዲሁም የማንበብና የመፃፍ ችሎታዬን እኮራባቸዋለሁ። እኔ ማንበብ መፃፍ የቻልኩት አንዳንድ ነገር ለመፃፍ አውራ ጣትህን አምጣ እያሉ ሲጠይቁኝ ስሜ ሲፃፍ እንዴት ነው? ብዬ በመጠየቅ

ቃላቱን ካየሁ በኋላ ቀላል መሆኑን ተገነዘቤ በራሴ በጉ ፈቃድ ቄስ ትምህርት ቤት በመግባት ተማርኩ። አባቴ ግን መሃይም ነበር። የትምህርትን ጥቅም ካወቅሁ በኋላ ሁለቱ ልጆቼ ቄስ ትምህርት ቤት ገብተው እንዲማሩ ሳደርግ ሌሎች ሁለቱን ደግሞ ዘመናዊ ትምህርት ቤት በማስገባት እያስተማርኳቸው ነው። እንዲገፉበትም ዓላማ አለኝ።

በድሮ ጊዜ ሴቶች ትምህርት ስላላገኙ ተጨቁነው ይኖሩ ነበር። አሁን ሴቶችም ወንዶችም ያወቁ ስለሆኑ እኩል ሆነዋል። የእግዚአብሔር ፈቃድ ሆኖ ዕድሜ ቢሰጠኝ ምኞቴ ልጆቼ ተምረው የተማሩትን ትምህርት ተግባራዊ ሲያደርጉ ማየት ነው።

## ማኅበራዊ ተቋማት

በየወሩ ስንበቴ የምንጠጣው ነፍሳችንን ለማዳን ስንል ነው። አንድ ሰው ሲሞት እያንዳንዱ ማኅበርተኛ አራት እንጀራና ወጥ በመያዝ በሃዘን ወደተጐዳው ቤት በመሄድ ሀዘን ያጐሳቆለውን ሀዘንተኛ ያጽናናል። ሌላው ምክንያት ደግሞ አስተዛዛኞቹ ነፍሱን ይማርልን ብለው ቢመርቁ የሞተው ሰው ዘላለማዊ ሕይወትን ያገኛል በማለት ነው።

እንደ ማኅበር ያሉት ነገሮች ግን ምርት እያጠረ በመምጣቱና ረሃብ በመከሰቱ እየተዳከሙ ሄደዋል። ሆኖም ፍፁም አልጠፉም።

| | |
|---|---|
| ሀጂ ዝቂ (ወ፤ እድሜ 57 ዓመት)፤ ቃዲ | ኢትዮ.9 |

አንጠረኛ? እሺ ፤ እኛ የራሳችንን ሥራ እንሰራለን፤ እነርሱም የራሳቸውን ፤ እርግጥ ነው ዝቅ አድርገን እናያቸዋለን፤ ይኸ አያጠራጥርም። ይህ ባህላዊ ጥላቻ ነው። ሰዎችን ይበላሉ ስለሚሉን እንፈራቸዋለን።

## የመቀራረብና የመከባበር ሁኔታ

አንጥረኛ እንደመሆኔ ገበሬዎች ወደ እኔ ይመጣሉ። ለምሰጠው ግልጋሎት በገንዘብ ሆነ በጉልበት ምን ሊያደርግልኝ እንደሚችል እጠይቀዋለሁ። እርሱም ገንዘብ ሊሰጠኝ እንደሚችል ወይም እርሻ ሊያርስልኝ ቃል ይገባና የጠየቀውን ሰርቸለት ረክቶ ይሄዳል። አንዳንድ መጥፎ ሰዎች ደግሞ ስለ ስራ የተሳሳተ አመለካከት ያላቸው፤ የእኛ ሰዎች ሌሎች ሰዎችን ይበላሉ ይላሉ። ሰው ሰውን እንደማይበላው መገንዘብ አለባቸው። ብረት በራሱ ሳይሠራ መሣሪያ ሊሆን እንደማይችል፤ ያለ መሳሪያም እርሻ ሊታረስ እንደማይችል ተረድተው ከእንደዚህ ያለ ንግግራቸው መቆጠብ ይኖርባቸዋል። ይህን የሚሉት ረጅም ምላስ ያላቸው ናቸው። [የተማሩት ግን ቡዳ የሚባል እንደሌለ ያምናሉ።]

> ብረት በራሱ መሳሪያ ሊሆን አይችልም።

በአካባቢያችን እስላሞችም አሉ። በውቂያ ወቅት እንድንረዳቸው ይጠሩናል። እኛም ማኅበር ወይንም ሰርግ ሲኖረን እንጠራቸዋለን። እነርሱም ስጦታ ፍየል ሳይቀር ይዘው ይመጣሉ። ያመጡትን ፍየል ራሳቸው ካረዱ በኋላ ምግባቸውን (እንጀራ ፤ ጠላ) አዘጋጅተው ከእኛ ጋር አብረው ይደሰታሉ። ሰው ከእኛም ሆነ ከእነርሱ በሞተ ጊዜ ስለምንከባበር ስራችንን ትተን ወደ ቀብሩ ስነ ሥርዓት እንሄዳለን። እንደ ቅሬ ሁሉ በመተባበር ፤ እህል በማምጣት አብስለን ሐዘንተኞችን እናስተናግዳለን። እነርሱም በእኛ ጊዜ እንደዚሁ ያደርጋሉ። ከእነርሱ ጋር ያለን ግንኙነት ይህንን ይመስላል።



መገናኛ

ከተማ የሚኖር የቤተሰብ አባል ወይም ጓደኛ ካለን ልንጠይቃቸው ስንሄድ ይጋብዙናል። እኛም [የማሽላ፣ የአተር፣ የባቄላ እሸት] ይዘንላቸው እንሄዳለን። እነርሱ ወደ እኛ መኖሪያ ከመጡ ደግሞ የፈላ ወተት ፣ የማርሸት ወይም ፍየል በማረድ እንጋብዛቸዋለን። አሁን አሁን ግን የግጦሽ ሳር ለከብቶች እየጠፉ በመምጣቱ ይህን የሚያደርጉ ጥቂት ሰዎች ናቸው።

ድሮ ሚስት ከችግራቸው እንዲላቀቁ በሬ ፣ ፍየል ፣ በቅሎ ወይም ፈረስ ይሸጥ ስትል ባል አይስማማም ነበር። የእርሷ ስራ በወፍጮ እህል መፍጨት ፣ ባሏ ከመንገድ ውሎ ሲመጣ እግሩን ማጠብ ፣ ምግብ ሲቀርብ ቆማ እጁን ማስታጠብ ነበር። አሁን ግን እኩልነት ስላለ እርሷ ሃሳብ ስታቀርብ በደስታ ይቀበላል። ስለሚያስብላትም እግሩን እንድታጥበው አይጠይቅም። እርሱ ራሱ ይታጠባል። የወፍጮዎችም መቋቋም በየምሽቱ እህል መፍጨቱን ስራ አስወግዶላቸዋል።

> አሁን እኩልነት ስላለ እግሩን ራሱ ይታጠባል።

## የመገናኛ አውታሮች

ወደ እርሻ ቦታዬ ለመሄድ ከሰፈር ለአንድ ሰዓት ከሃያ አምስት ደቂቃ ርቄ መሄድ ይኖርብኛል። እኔ የምኖረው አረባል ሲሆን የእርሻ ቦታዬ ደግሞ ጉራንቆባ ነው። በርቀት ካለው ገረገራ ከሚባለው የገበያ ቦታ ለመድረስ የእርሻ መሣሪያዎች ፣ ለዘር የሚሆን እህል ይገፌ በሬዎቼን እየነዳሁ አራት ሰዓት ከሃያ ደቂቃ

በእግር መጓዝ ይኖርብኛል። በልደት [በገና] ወደ ላሊበላ ቤተ ክርስቲያን ለመሄድ ደግሞ ስምንት ሰዓት ተኩል በእግር መጓዝ አለብን። ቢልባላ ከሚባለው ቤተ ክርስቲያን ሄደን ፀሎት ለማድረስ ከፈለግን ከዘጠኝ እስከ አስር ሰዓት በእግር መጓዝ ይኖርብናል።

ቀደም ሲል ጉንደርን ፣ ባህር ዳርን ፣ ጋይንትን ፣ አዲስ አበባን ሳይቀር አይቼ አላውቅም ነበር። የቻይና መንገድ ከተሠራ ወዲህ ግን በተሽከርካሪ በመጓዝ ሁሉንም ለማየት በቅቻለሁ። ይህን በማድረጌም ደስተኛ ነኝ።

## የህብረተሰብ ጤና

በድሮ ጊዜ ሰው ሁሉ ጤናማ ነበር። አሁን ግን በከተማዎች ኤድስ፣ በገጠር ደግሞ የደም ተቅማጥና ወባ ተንሠራፍተዋል። ይህ እንዴት እንደሆነ ይደንቀኛል። ሁሉም ታማሚ ስለሆነ ወደ ገበያ የሚወጣ የለም። ጊዜው ይሁን ወይም ሌላ ነገር ለማወቅ አልቻልኩም። ወላጆቼ እንደነገሩኝ እኔ ሕፃን በነበርኩ ጊዜ እንደዚህ አይነት ወረርሽኝ ገብቶ ነበር። መንግስት ይህን ወረርሽኝ ለማስወገድ በእያንዳንዱ ቤት ዲዲቲ ረጭቶ ወረቀት ይለጥፍ ነበር። ይሁን እንጂ ነፍሳቱ መድሃኒቱን በመልመዳቸው ከተደበቁበት ቦታ ከየሚካው እየወጡ ሰዎችን ያጠቁ ነበር።



**የምግብ ዋስትና**

በአባቶቻችን ጊዜ በግብረ ስጋ ግንኙነት የሚተላለፉ በሽታዎች ጨብጥና ቂጥኝ ብቻ ነበሩ። እነዚህም ስለጠፉ ሰዎች ጤናማ የግብረ ስጋ ግንኙነት ያደርጉ ነበር። አሁን ግን በሰውነት ላይ የሚወጣ ሽፍታና ኤድስ አለ። አሁን አንድ ሰው ከበሽታ ሊድን የሚችለው የግብረ ስጋ ግንኙነት ካላደረገ ብቻ ነው። አንድ ሰው ወፈፌ ሆኖ ሚስቱን በመደብደብ ከፈታና ከሌላ ሴት ጋር የግብረ ሥጋ ግንኙነት ከፈፀመ በኤድስ ተለክፎ ይሞታል። ይህ ኤድስ የተባለ በሽታ መድሃኒት እንዳለው ስንጠይቃቸው መድሃኒቱ የግብረ ሥጋ ግንኙነት አለማድረግ ነው ይሉናል። ይህም በሃዘን አንገታችንን ያስደፋናል።

## <u>የምግብ እጥረትና ረሀብ</u>

በእኛ መንደር ረሃብና ድርቅ የጀመረው በ1984 ዓ.ም ነው፣ በዚያን ጊዜ ሰዎች ተሰደው ነበር። ከ1985-1988 ባለው ጊዜ ደግሞ መሬቱ ምርት [እንደገና] መስጠት ጀመረ ብለው ወደ ቀያቸው ተመለሱ። ይሁን እንጂ በ1995 እና በ1996 ረሀብ እንደገና ተመለሰ።

> ረሀብን የተቋቋምነው ፍየሎቻችንን እና በጉቻችንን በመሸጥ ነው።

የምግብ እጥረት ሲኖር አንድ ሰው ሁለት እንጀራ ካለው አንዱን ፣ አንድ እንጀራ ካለው ደግሞ ግማሹን ይበላል። ሰውነቱ እየገረጣና እየመነመነ ይሄዳል እንጂ አይሞትም፣ ረሀብ ከሆነ ግን ምንም የሚቀምሰው ስለሌለ በሶስት ቀን ጊዜ ውስጥ ይሞታል። ረሀብን ልንቋቋመው የቻልነው ፍየሎቻችንንና በጉቻችንን በመሸጥ፣ ትንሽ ትንሽ በመነገድ ፣ በመበደር ፣ ከእኛ

ሻል ካሉት ወንድሞቻችን ድጋፍ በመጠየቅ ነው። ችግሩን አሁን እየተቋቋምነው ያለነው በዚህ መልክ ነው።

ሽንብራና ሱፍ ዘርተን ለውጠን እንጠቀምባቸው ነበር፤ የተለያዩ ፍራ ፍሬዎችን እንደ ሎሚ ፤ ብርቱካን ፤ ኮምጣጤ ፤ ፓፓያ በመትከል ደግሞ እንበላ ነበር። እርግጥ ነው ፤ ስጋና ቅቤን የመሳሰሉ ጥሩ ምግቦች አሉ። ነገር ግን እጅ ሲያጥር እነርሱን በመተው ወደ ሽሮ በእንጀራ ትመለስና ወደ ስራ ትሄዳለህ። ድሮ ማር ፤ ቅቤና ስጋ በሚበላበት ጊዜ ሰውነታችን ያማረ፤ የጠነከረና ጤናማ ነበር። አሁን ግን ሽሮ በእንጀራ ሲበላ ፤ የምግቡ ጥራት እየቀነሰ መጥቷል። ሰውነት እየመነመነ ይሄዳል። ይህ ክስተት በህፃናት ላይ ብቻ ሣይሆን ከ44-45 አመት እድሜ ባላቸው ሰዎች ላይም ይታያል። የሚበላው የምግብ አይነት እየቀነሰ በመምጣቱ ሰውነት እየተዳከመ ሄዷል።

<u>ለምለም</u> ኢትዮ. 3

ለምለም የ67 ዓመት መነኩሴ ስትሆን ነዋሪነቷ ወይናደጋ ነው።

ምግብ እየተበላ እንግዳ ከደረሰ መጋበዝ ባህላችን ነው በማለት ቃለ መጠይቅ አቅራቢውን አብሮ እንዲበላ ጋበዙት፤ እንደ ቃለ መጠይቁ አቅራቢው አገላለጽ ፤ ለጥያቄው በመታጨታቸው ፊታቸው በደስታ ብሩህ ሆኖ ይታይ ነበር። በአሁን ጊዜ የአባቶቹን ታሪክ ለማወቅ ፍላጐት ያለው የለም በማለት ነበር ገለፃውን የጀመሩት፤ <<ወጣቱ እንኳንስ ስላለፈው ታሪክ ሊያውቅ ቀርቶ ታላቁን አያከብርም፤ የእነርሱን ትዕዛዝ አይቀበልም>> በማለት ካጠገባቸው ያለውን ትንሽ ልጅ ወደ ጉረቤታቸው በመላክ

በአካባቢያቸው ጫጫታ የሚያሰሙትን ሴቶች ደግሞ ገዛም እንዲሉ አዘዙአቸው።

በድሮ ጊዜ የህዝቡ ብዛት አነስተኛ ፤ መሬቱም ምርታማ ነበር። መሬታችንን ለሁለት በመክፈል አንዱን ክፋይ በማረስ ፤ ሌላውን ለሚቀጥለው ዓመት እንዲቆይ እናደርግ ነበር። ወደ ገበያ ሄደን ሶስት ላዳን እህል በህምሳ ሳንቲም እንሸምት ነበር። አሁን ግን የምንሸምተው በአነስተኛ ቆርቆሮ ነው። ሕዝብም እየበዛ በመምጣቱ ከመንግስት እየተመፀወተ ነው ኑሮ እየገፋ ያለው። ድሮ ምንም በሽታ ቢኖርም እንደ አሁኑ ድንገተኛ ሞት የለም። ብዙም የሚወልድ አልነበረም፤ ሰዎችም እርስ በእርስ ይተሳሰቡ ነበር። በአሁኑ ጊዜ ወንድም ወንድሙን ፤ እህት እህቱን አይወድም። የእርሻ መሬቱ በጉርፉ በመታጠቡና አፈሩም በመሸርሸሩ ምርት ስለማይሰጥ ሁሉም የመንግስት እጅ እያየ እንዲኖር ተገድዷል።



<<አፈሩ እየታጠበ በመሄዱ መሬቱም ምድረ በዳ ሆኗል>>



የመሬት ገፅታ

## መሬት፣ እየቀነሰ የመጣ ሀብት

ድሮ ቁጥቋጦዎችን መንጥሮ በማቃጠል የሚገኘውን መሬት በአንድ ጥማድ በሬ አርሶ ከተለመደው ምርት እጥፍ እህል ተመርቶ (ከመሬት ውስጥ የሚገኝ) የእህል ጉድጓዶችን ሙሉ ነበር። ዛሬ መሬት እንደ ሌጦ ሆኗል፣ ምርታማ አይደለም። ሰፊ መሬት ታርሶ አንድ አቁማዳ እህል እንኳ አይገኝም። ድሮ መሬት ከአባት የሚወረስ ስለነበረ፣ ባል ሚስት ለማግባት ከፈለገ ዘሩን በመቁጠር፣ መሬት አላት፣ የእነ እንቶኔ ልጅ ናት ብሎ ያገባ ነበር። አሁን ግን ኑሮአችንን የምንገፋው ጠላና አረቄ እየሸጥን ነው። አሁን መሬቱ አሸዋማ ስለሆነ ያለ አረም፣ እንክርዳድና ግንጫ አያበቅልም። ድሮ ግን አረሙ እንኳ በብዛት ባይነቀልም በቂ ምርት ይገኝ ነበር። አሁን ግን ከብቶችም በጥሩ ሁኔታ አይደሉም። እናቶችና አባቶች እርስ በእርስ አይረዳዱም። ምን ይሆን ምክንያቱ? ድህነት ነው!

> ዛሬ መሬት እንደ ሌጦ ሆኗል፣ ምርታማ አይደለም

በድሮ ጊዜ ከብቶች የትም ሄደው በየኮረብታውና ጫካው ይለቅሙ ነበር። አሁን ግን የተወሰነው ክፍል በመንግስት ለጫካ ተብሎ ስለተከለለ፣ ከአንድ ቦታ ወደ ሌላ ቦታ ተዘዋውረው ለመጋጥ አይችሉም። ባለከብቶች ከብቶቻቸውን የሚመግቧቸው በየእርሻ ማሳዎች ድንበር የሚገኘውን ሳር በማጨድ ነው።

ጥንት የከብቶች በሽታ ይከሰት የነበረው በየአራት ወይም አምስት አመቱ ነበር። ዛሬ ግን የግጦሽ መሬት በመጥፋቱ እንስሳቱ በረሃብ እያለቁ ናቸው። የሕዝብ ብዛት መሬቱን እያጣበበው

> የድግሱ ስሩት መጠን ተለውጧል፤ ባህሉ ግን አሁንም ጥብቅ ነው።

መጥቷል። ይህም በመሆኑ መሬት በገመድ እየተለካ እየተከፋፈለ ነው። በዚህም ምክንያት እንኳንና ለከብቶች ግጦሽ የሚሆን መሬት ለማግኘት ይቅርና ለእግር ማሳረፊያ የሚሆን ለማግኘት አይቻልም። አንዳንድ ሰዎች የድሮ ልምድ አልለቃቸው ብሎ ከብት ለማርባት በሚሞክሩበት ጊዜ ፤ ከብቶቻቸው ወደ ሌላ ይዞታ ሲገቡ ጥል እየተፈጠረ ሰዎች እየተገዳደሉ ነው።

## የፀረ ሰብል ተባዮች መራባት ፤ የዱር አራዊት መጥፋት

በአሁኑ ጊዜ በጣም ብዙ ፀረ ሰብል ተባዮች አሉ፤ እንደደገዛ፤ ድሪ ያሉ ቡቃያ የሚያወድሙ ናቸው። ፈንጠራ ደግሞ ገዘናብ ካቋረጠ እህል የሚያወድም ተባይ ነው። መንግስት በግብርና ቢሮው አማካኝነት ፀረ-ተባይ መድሃኒት ወደ ቆላ ፤ ደጋው አካባቢ እየላከ በመርጨት ላይ ነው። ድሮ ደጋዛ የሚባል ተባይ አልነበረም። ብቻ በአራትና በአመስት አመት በሰማይ እየበረረ የሚመጣ አንበጣ ነበር። ይህንም ልብሶቻችንን ወደ ላይ ዘርግተን ስናውለበልብ እየሸሸ ስለሚሄድ እህሉን ሊያጠፉብን አይችልም ነበር። ከዚያም በኋላ ከመሬት ላይ ፈጽሞ አይታይም። ቀደም ሲል ብዙ ጫካዎች ስለነበሩ አንበሳ ፤ ነብር፤ ጅብ ፤ ድኩላ ይኖሩበት ነበር። አሁን ግን ጫካ የምትባል ትንሽ ጥብቅ ደን ብቻ ናት የምትታየው። ቁጥቋጦም ሆነ ዛፎች የሉም።


በድሮ ጊዜ ቅቤና አይብ እንበላ ስለነበር የጤና ችግር አልነበረብንም። አሁን ግን በደንብ ስለማንመገብ ሰውነታችን መከላከያ እያነሰው ለበሽታ እየተጋለጥን ነው። የመንግስት ወታደሮች ስላሉ የጤና ጣቢያዎች እየተገነቡ ናቸው። ይህም ሆኖ በሆድ ቁርጠትና በራስ ምታት ህመም እየተሰቃየን ነው። ለዚህም መንግስት ምስጋና ይግባውና ከውጭ የሚያስመጣቸው ክኒኖች እየተጠቀምን ነው።

## <<የመቄት ሰዎች በጣም ኃይማኖተኞች ናቸው>>

የተማረ ሰው ብዛት እየጨመረ ሲሄድ አካባቢያችን እየለማ ይሄዳል የሚል እምነት አለን። ድሮ ሰንበቴ ሲኖረን ለነፍሳችን ስንል ሁለት ወይም ሦስት ላዳን ቆሎ ቆልተን ወደ ቤተ ክርስቲያን በመውሰድ ድሆችን እንመግብ ነበር። የቅድስት ማርያም ክብረ በአል ጊዜም ድግስ በየቤታችን ደግሰን በደማቅ ሁኔታ እናከብር ነበር። ዛሬም ቢሆን የምግብ እጥረቱ ቢይዘንም ዳቦ መጋገርም ሆነ ለድሆች መመገባችንን አል ተውንም። ምንም እንኳ ማኅበር እየቀነሰ ቢሄድም ወጣት ተማሪዎች እራሳቸውን በመንፈሳዊ ቡድን አደራጅተው ቤተ ክርስቲያን በማገልገል በመጾም ላይ ናቸው። ይህ ድሮ የተለመደ አልነበረም።

> ቅቤና አይብ
> እንበላ ስለነበር
> የጤና ችግር
> አልነበረብንም።

ጥንት ወደ ቤተክርስቲያን ሄደው ፀሎት የሚያደርሱት፣ የቅዱሳንን ቀን የሚያከብሩ፣ ማኅበር የሚደግሱ ትላልቅ ሰዎች ብቻ ነበሩ፣ አሁን ግን ወጣቱ ያገባም ፣ ያላገባም ወደ ቤተ ክርስቲያን በመሄድ ጸሎት በማድረስ የቅዱሳን ቀን ከሆነም ያከብራል።



ቤተሰባዊ ሕይወት

በአሁኑ ጊዜ ክርስቲያን ሆኖ በማኅበርና በዝክር የማይሳተፍ፣ ታቦት ሲወጣ የማያጅብ የለም።

የመቄት ሕዝብ ኃይማኖት አጥባቂ ነው። ብዙ ገዳማት፣ ቤተ ክርስቲያኖችና መነኮሳት የሚኖሩበት ነው። በላሊበላ 12 አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ። ይምርሃ በሚባለው ቤተ ክርስቲያን የሞቱ ሰዎች አስከሬን ሳይፈራርስ የተቀመጠበት ፣ ሰዎች ሄደው ጸሎት እያደረጉ ሲማፀኑት ከሃጢያታቸው የሚፀዱበት ነው። ዛሬ ሀጢያታችን እየበዛ ስለሄደ በእግዚአብሔር ዘንድ ተደማጭነታችን እየቀነሰ ሄዷል። ደብረ አውነ አኖር የሚባለው ደብር ደግሞ ታቦቱ የተቀመጠው ጣሪያ በሌለው ቦታ ሆኖ ዝናብ ግን አይጥልበትም። ቦታው በጥሩ አጥር የተከበበና ለሴቶች የተከለከለ ቅዱስ ቦታ ነው። በጫካው ውስጥ ባህታውያን ከሰሌን የተሰሩ ባርኔጣና እጀ ጉርድ ልብሶች የአካላቸው መሸፈኛ አድርገው ቅጠሎችን እየተመገቡ ይኖራሉ።

<u><<ፍቅረኞች ሚስጥራቸውን አጥብቀው መያዝ አለባቸው>></u>

ጋብቻ የተከበረ ነበር። ልጅቷ ሳታውቅና ሳትነገር ለጋብቻ ወላጆች ብቻ ይጠየቁ ነበር። ለሰርጉ የሚደረገው ድግስ ብክነት የተሞላበት ስለነበረ ለዝግጅቱ ከአራት እስከ አምስት አቁማዳ እህል፣ ሰንጋዎችና ሙክቶች ይታረዱ ነበር። በድሮ ጊዜ ያልተፈቀደ ግንኙነት ነውር ነው። ፍቅረኞች ሚስጥራቸውን አጥብቀው ካልያዙ ፣ ይህን ያልተፈቀደ ግንኙነት እናት ፣ ወንድም ፣ አክስት፣ አጐት ከሰሙ ሰውየውን እንደሚገድሉት ይዝቱበታል፣ ሴትየዋን ደግሞ

ይገርፏታል። ከጋብቻ በፊት ወይም ከጋብቻ ላይ የግብረ ስጋ ግንኙነት ማድረግ ፍጹም የተከለከለ ነው። የፈታች ሴትም ብትሆን ያላትን የወንድ ግንኙነት ደብቃ መያዝ አለባት። በአሁን ጊዜ ግን ሴቶች እጮኛቸውን የሚመርጡት በትምህርት ቤት ሆኖ ለጋብቻ ሲጠየቁም ወላጆች ብቻ ሳይሆኑ እነርሱም ጭምር ናቸው። ልጆች ከወላጆቻቸው ቁጥጥር ውጭ ስለሆኑ ከጋብቻ ውጭ ልጆች እየተወለዱ የህዝብን ቁጥር እየጨመሩት ነው።

በድሮ ጊዜ አንድ [ሴት] ከባሏ ጋር ለመለያየት ከፈለገች ሐሳቧን ትገልጽለትና ፍቺው ይፈፀማል። እርሱም ከፈለገ እንደዚሁ ያደርጋል። ዛሬ ግን ፍቺ ለመፈፀም ወደ ፍርድ ቤት ሄዶ እየተጨቃጨቁ ጊዜን ማባከን ፤ ባል ቤቱን ልቀቂልኝ ሲል እምቢ በማለት ፤ መንግስት ካልፈቀደ አልፈታህም፤ እርሱም እንደዚህ በማለት ሙግት ይገጥማሉ። በቤተሰብ ስምምነት የለም። ሰውየው ታታሪና ሠራተኛ ሆኖ እየነገደ ገንዘብ ካገኘ ፤ ሚስቱ ሰነፍ ትሆንና ምንም ድጋፍ አትሰጠውም። እርሷ ታታሪ ስትሆን እርሱ ገንዘብ ለጋለሞታ የሚበትን ይሆናል። ከድህነታቸው በተጨማሪ ትልቁን ከትንሹ ለመለያየት አዳጋች የሚሆኑ በራስ በራስ የተወለዱ ልጆች ያሳድጋሉ። ይህም በመሆኑ ከቁጥጥር ውጭ የሆነ የህዝብ ብዛት አለ። አንድ ቀን ወደ ቤተ ክርስቲያን ሐኪም መጥቶ የህዝብ ብዛት እድገት ለመቆጣጠር መርፌ እንዲወጉ ጥሪ አድርጓል።

**ሞት/ሙቱት/**

በህዝብ ብዛት ይሁን፤ ወይም መንገዱ በመሠራት ወይም የሰዎች ከቦታ ቦታ እንቅስቃሴ፤ ምክንያቱን በውል ለይቼ

አላውቀውም፤ በአሁኑ ጊዜ እንደ ጨብጥ ያሉ በሽታዎች በዝተዋል። አንዳንድ በሽታዎች በትንፋሽ የሚተላለፉ አሉ። መድሃኒት መዋጥ ሲቻል እንደ ኤድስ ላለው ...

ጥንት በድንገት ስንታመም ከቅጠል የተዘጋጀ ባህላዊ መድሃኒት እንወስድ ነበር። ላምና በሬያችንን ሸጠን ሁለት ሳምንት ያህል በእግራችን ተጉዘን ቆቦ ፤ ትግራይ ወይም ጐንደር እንደርስ ነበር። አሁን ግን በመኪና ተሳፍረን በመሄድ መድሃኒት እናገኛለን። ምንም እንኳ ሞት እንዳሁኑ ባይበዛም ድሮ በረሃብና በጥም በጉዞ ላይ እንዳለን እንሞት ነበር። በአሁኑ ጊዜ ሰዎች በቀብር ተሰላችተዋል። በቀድሞ ጊዜ በሙሾ ላይ የሚደረጉ ግጥሞች አሳዛኝ ነበሩ። አንደኛው እንዲህ የሚል ነበር።

አ! አ! እግዚአብሔር ለእህቶቼ ጽናቱን ይስጣቸው ፤
እግዚአብሔር ለወንድሞቼ ጽናቱን ይስጣቸው፤
አሁን የቀን ጅብ ልጆቼን እንዳይበላቸው።

ሽማግሌዎች ጣልቃ ይገቡና እንዲህ ይላሉ፡-

እኛ በጣም አዝነናል
አሁን ይበቃል፤
አይኖች አጥንት ስለሌላቸው
ቀልጠው ውሃ ይሆናሉ
ሟሙተው ይደርቃሉ

አሁን ግን በአርባ ወይንም በሃምሳ ብር ሙያተኛ የተባሉ አስለቃሾች ቢቀጠሩም በቂ ችሎታ ግን የላቸውም። ድሮ ዘመዶች የሆኑ ምንም ገንዘብ ሳይከፈላቸው ሙሾዎችን እየደረደሩ አልቅሰው ያስለቅሱ ነበር። አሁን ሰዎች ከቀን ወደ ቀን እየከሱ ፤ እየመነመኑ ፤

በቁማቸው ሲራመዱ አጥንታቸው እየተቆጠረ ቆይተው ይሞታሉ። ዛሬ ብዙ ሞት አለ።

የሐዘን ግጥሞች (ሙሾ) የለም።

<u>ሀጂ ዝቂ</u> ኢትዮ . 9

ሀጂ ዝቂ 57 ዓመት ያላቸው እስላምና ቃዲ ሲሆኑ በጨርቆስ ነዋሪ ናቸው። በህብረተሰቡ ውስጥ ያላቸውን ተሳትፎና የሥራ ኃላፊነት በመናገር ፣ አልፎ አልፎ የሚከሰተውን ረሃብ ለመቋቋም ሰዎች የተከተሏቸውን ስልቶች ይገልጻሉ።

[እኔ የተወለድኩት] የጣሊያን ወረራ ሲጀመር ነው። በዚያ ጊዜ ማር ፣ የሚታለቡ ላሞች፣ የሚረቡ ፍየሎች ስለነበሩን ስጋም ስለምንበላ የህዝብ ብዛትም ትንሽ ስለነበር ጥሩ ሕይወት ነበረን። ብዙ ዛፎችና ጫካዎች ስለነበሩ ጉርፉን ይከላከሉ ስለነበር መሬቱ ምርታማ ነበር። መሬትም ለተወሰነ ጊዜ ሳይታረስ አርፎ ከቆየ በኋላ ነበር ዳግመኛ የሚታረሰው። አሁን ግን ሕዝቡ እያደገ መምጣት፣ የዛፎች መመንጠር፣ የመሬቱ በግጦሽ ብዛት መራቆት ፣ የጫካዎች (የደኖች) መጥፋት መሬቱን በጉርፍ እንዲታጠብ ስላደረገው ምርታማነቱ ቀንሷል።

ቀደም ሲል አንድ ቤተሰብ እስከ 10 ማሳዎች ይኖሩት ነበር። አሁን ግን የሕዝብ ቁጥር ስለጨመረ የእያንዳንዱ ቤተሰብ ይዞታ ወደ ሦስትና አራት ማሳዎች ወርዷል። እንዲያው አሁን ካለው

> በላቸው ፣ (ወ. 62 ዓመት) አንጥረኛ ኢትዮ. 18
>
> በሀይለስላሴ ዘመን ምንም የእርስ በርስ ጦርነት ሳይኖር ሰላም በመኖሩ ነጋዴዎች ምንም በሌለበት ውድማ መሬት የጨረቃ ብርሃን እያዩ ተጉዘው ሌሊቱን በጨረቃ ብርሃን አሳልፈው ጉዳያቸውን ፈጽመው ይመለሱ ነበር ። በኋላ ግን ነገሮች እየተበላሹ መጡ።

ይዞታችን የሚያንስ [ሌላ] መሬት ክፍፍል ይኖራል የሚል ስጋት አለን። በአንዳንድ ሰፈሮች መስኖ በመጠቀም በርበሬና ቡና ማልማት ተጀምሯል። አሁን ግን የመስኖው ተጠቃሚ እየጨመረ በመምጣቱ ለእያንዳንዱ ገበሬ የሚደርሰው መሬት እየቀነሰ ስለመጣ ምርታማነቱ ቀንሷል። አሁን የመሬት ጥበት ስላለ በመስኖ የሚለማው በጣም አነስተኛ ነው።

ድሮ የነበሩት አንበጣና ጀሚ የተባሉ ተባዮች ነበሩ። በአንበጣ የተበላው መልሶ የሚቆጠቁጥ ሲሆን ፣ ጀሚውን ደግሞ ጨፍጭፈን እናጠፋው ነበር። በአሁኑ ጊዜ ግን ተባዮች በዝተዋል። ቅዱስ ቁራን እንደሚለው ሰዎች አመንዝራነትንና ስርቆትን እየፈፀሙ ከሄዱ እንደ አንበጣና ደፍሪ ያሉ ተባዮች እየበዙ እንደሚሄዱ ነው። ተባዮች እየበዙ በመሄዳቸው የአተርና የምስር ምርቶች ቀንሰዋል።

## ብዙ ገንዘብ ፣ የመግዛት አቅሙ ግን አነስተኛ

በኃይለስላሴ ዘመነ መንግስት ሁሉም ነገር ርካሽ ስለነበር አባቶቻችን ሁለት ቁና በርበሬ በአንድ ብር ይገዙ ነበር። በደርግ ጊዜም ቢሆን ትንሽ ወደድ ይበል እንጂ ገንዘብም ስለሚገኝ በቀላሉ ይገዛ ነበር። በዚያን ጊዜ ገበሬዎች በማረስ ፣ ሸማኔዎች ልብስ በመሥራት ፣ አንጥረኞች መጣሪያዎችን በማዘጋጀት ፣ እያንዳንዳቸው እንደ ስራ ድርሻቸው በመሥራት በቂ ገቢ ነበራቸው። አሁን በኢህአዴግ ጊዜ ግን ብዙ ገንዘብ አለ፤ የሚገዛበት ግን ትንሽ ነገር ነው።